
# የአዲስ አበባ ስነ ምግባርና ፀረ- ሙስና ኮሚሽን

# የሙስና ፅንሰ ሃሳብና መከላከያ ስልቶች

## (የማሰልጠኛ ሞጁል)

## በኮሚሽኑ የተዘጋጀ



**ሙስና ስጋት የማይሆንባት አዲስ አበባን እንፈጥራለን!**

**ህዳር 2016 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

## መግቢያ

የአዲስ አበባ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በሥነ-ምግባር እና በሙስና መከላከል ዙሪያ የተለያዩ የማሰልጠኛ ሞጁሎች በማዘጋጀትና ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በጠቀም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን እንዲሁም የተቋማት ሰራተኞችን በስፋት እያሰለጠነ ይገኛል፡፡
ይህ ሞጁል የሙስና ፅንሰ ሃሳብ እና መከላከያ ስልቶች የሚል ርዕስ የያዘ ሲሆን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሞጁሉ ከተዘጋጀበት ዓላማ አኳያ አሰልጣኞች ተቋማዊ መልክ የያዘ ውጤታማ ስልጠና መስጠት እንዲችሉ የሚያግዟቸው የአጠቃቀም ማንዋል ተዘጋጅዋል፡፡በዚህ መሰረትም የቀረቡት ሞጁሉ የሚከተሉት ሁለት ክፍሎች ይይዛል፡፡

- **ክፍለ አንድ፡- የሙስና ጽንሰ ሃሳብ፣**
- **ክፍል ሁለት፡-  የሙስና መከላከያ ስልቶች ናቸው፡፡**

ይህ የሥልጠና ሞጁል በዋናነት ሁሉንም የመንግስት ተቋማት እና ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች በተመላከተው ርዕስ ጉዳይ ላይ እውቀት ለማስጨበጥ እና የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ከፍል ሰራተኞችን አቅም፣ እውቀትና ክህሎት በማሰደግ ሰልጥነው እንዲያሰለጥኑ እና እንዲተገብሩ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

የዚህ ማሰልጠኛ ሞጁል ጥቅል አላማ ሰልጣኞች የሙስና ፅንሰ ሃሳብንና የሙስና ባህሪያትን በመረዳት በየተቋሞቻቸው እንዲከላከሉ እና የመከላከያ ስልቶችን እንዲተገብሩ ለማስቻል ነው፡፡ አሰልጣኞች እነዚህን ሞጁሎች ከአጠቃቀም ማንዋሉ ጋር በማቀናጀት ቢሰሩ ውጤታማ ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ሞጁሎቹ በዚህ መልክ ከመሰናዳታቸው ውጭ ከዚህ በፊት ሞጁሎች ማሻሻያ ሲደረግባቸው

**የተጠቀሱት ዋና ዋና ነጥቦች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡ እነሱም፡-**

- ከዓላማ አጻጻፍ አንጻር ተገቢነት ይጎድላቸው የነበሩ ዓላማዎች ከሠልጣኞች የሚጠበቁ ውጤቶችን በግልጽ በሚሳዩ እና መለካት በሚችሉ አገላለጾች መተካታቸው፣
- ከይዘት አንጻር ግልጽነት ለሚጎድላቸው ይዘቶች ተጨማሪ ምሳሌዎች፣ መልመጃዎች፣ ኬዞችና የማጠናከሪያ ሃሳቦች መታከላቸው፤

- የምሳሌዎች፣ የመልመጃዎችና የማጠናቀሪያ ሃሳቦች ተጨባጭነትና ወቅታዊነት ለመጠበቅ አብዘኛዎቹ መልመጃዎች፣ ምሳሌዎችና ኬዞች በተግባር ከተፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች ወይም ከታዩ ብልሹ አሰራሮች ወይም ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ ተቀድተው ለማስተማሪያነት በሚያመች መልኩ እንዲቀርቡ መደረጋቸው እንደተጠበቀነው፡፡

**የሞጁሎቹ አጠቃቀምና አቀራረብ**

የማሰልጠኛ ሞጁሎቹ ለተጠቃሚው የተመቻቹ (user friendly) እና አሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ለዚህም ሰልጣኞች ቀደም ሲል ካላቸው እውቀት በመነሳት እየተወያዩ፣ እየተከራከሩ ወደ.ጋራ መግባባት እንዲደርሱ የተለያዩ ተግባራት፣ መልመጃዎችና ኬዞች ቀርበዋል፡፡ ተግባራቱም መከናወን ያለባቸው በሠልጣኞች ሆኖ አሠልጣኞች የማመቻቸት (facilitation) ሚና ይኖራቸዋል፡፡

በሥልጠና አቅርቦት ወቅት አሠልጣኞች ለመነሻ በየክፍለ ትምህርቶቹ የቀረቡትን የይዘት ማብራሪያዎች ለሠልጣኞች ከማብራራታቸው በፊት በየትምህርቱ መጀመሪያ ላይ ለመነሻ የቀረቡትን ተግባራትና መልመጃዎች ሠልጣኞቹ በርዕስ ጉዳዮቹ ዙሪያ ያላቸውን ቀደምት እውቀት ተጠቅመው እንዲያከናውኗቸውና እንዲወያዩባቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አሠልጣኞች ክንውኑን ከትምህርቱ ዓላማዎች፣ ከተሠጡት የይዘት ማብራሪያዎችና ዋናዋና ነጥቦች አኳያ በማየት አቅጣጫ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

ሞጁሎቹ ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ በየክፍለ ትምህርቶቹ የተለያዩ ኬዞች ቀርበዋል፡፡ አብዘኞቹ ኬዞች በተግባር ከተፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች ወይም ከታዩ ብልሹ አሰራሮች ወይም ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ ተቀድተው ለማስተማሪያነት

በሚያመች መልኩ ተዘጋጅተው የቀረቡ ናቸው፡፡ ከቀረቡት ኬዞች ስር ለመወያያ መነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች አንድ ቁርጥ ያለ መልስ ላይኖራቸው ይችላል፡፡

ይልቁንም ሰልጣኞች ከልምዳቸው፣ ከቀደመ ስልጠናቸውና ካዳበሩት ንባብ እርስበርስ ልምድ እንዲለዋወጡበት ታስበው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ የአሰልጣኞች ሚና የዕውቀት ባለቤትነት/ምንጭነት ሳይሆን ስልጠናውን የማሳለጥ ድርሻ ብቻይሆናል፡፡

ሞጁሎቹ ይዘቶችን፣ የመወያያ መልመጃዎችንና ተግባራትን ለማቅረብ የሚከተሉት ዋና ዋና ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፡፡

- **የቡድን ወይይት** (Group discussion)

ሰልጣኞች በተነሱ ጭብጦች እና በቀረቡ ጥያቄዎች ዙሪያ ካላቸው ቀደምት ልምድ እና በስልጠናው ከቀረበው ትምህርት ተነስተው አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ፣ መከላከያ ስልት እንዲነድፉ፣ የሰረቱን ለሰልጣኞች እዲያቀርቡ እና ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ለማድረግ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው፡፡ በተጨማሪም የቡድን ውይይት የተለያዩ ኬዞችን በማቅረብ የሰልጣኞችን እይታና አመለካከት የምናሰፋበት የስልጠና ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞችን በትንንሽ እና በትልልቅ ቡድን በማወያየት ክህሎታቸውንና አመለካከታቸው እንዲያሳድጉ ማድረግ ይገባል፡፡

- **የአእምሮ ጎዳ ማንኳኳት** (Brainstorming Sessions)

የአእምሮ ጎዳን ማንኳኳት ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በተቀመጡ ጥያቄዎች መሰረት ቁልፍ ለሆኑ ሃሳቦች ሰልጣኞች ከቀደምት እውቀትና ልምዳቸው ተነስተው ሃሳባቸውን እንዲገልጹ የማነሳሳት ተግባር ነው፡፡

• **ገለጻ** (Presentations)፡

ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ወይም ሃሳቦች ዙሪያ ሰልጣኞችን ለማገዝ በአሰልጣኞች አማካኝነት የሚሰጥ ገለፃ ወይም ማብራሪያነው፡፡

- **ሚና ጨዋታ** (Role play)

በትንንሽ ቡድን በመሆን ሰልጣኞች በቀረበው ኬዝ መሰረት የሚሰጣቸውን ሚና በመጫወት በተግባር የሚሆኑ ነገሮችን በድራማ መልክ ለማስገንዘብ እንዲረዳ ታስቦ የቀረበ ነው፡፡

• **ኬዝ ጥናት** (Casestudies)፡

የኬዝ ጥናት በተግባር በተፈጸሙና እንደምሳሌ በቀረቡ ጉዳዮች ላይ ሰልጣኞች በቡድን፣ በጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ታስቦ የቀረበ ስልት ነው፡፡
አሰልጣኞች እንደ ይዘቶቹ ሁኔታ፣ እንደመለማመጃዎቹ ጠባይና እንደቀረበው ትእዛዝ ከላይ የቀረቡትን ስልቶች ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጅ አሰልጣኞች በአማራጭነት ከቀረቡት የሥልጠና ተግባራት ወይም መልመጃዎች እና የአቀራረብ ሥልቶች ውጭ የተሻለ ዘዴ አለ ብለው ያመኑበትን ለመጠቀም ይችላሉ፡፡

### የሙስና ጽንሰ ሀሳብ

አጭር መግለጫ ይህ ሞጁል አጠቃላይ ስለሙስና ምንነት እና የሚያስከትለው ጉዳት የሚያትት ሲሆን በመንግስት ተቋማትና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችና የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን የሙስና መካለከል አቅም ለማሳደግ የተዘጋጀ ነው፡፡

## የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ

ሰልጣኞች የዚህን ሞጁል ስልጠና በሚገባ ሲያጠናቅቁ የሙስናን ምንነት በመረዳት ሙስናን በመከላከሉ ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ ያበረክታሉ፡፡

## ክፍል አንድ፡ የሙስና ፅንሰ ሀሳብ

### መግቢያ

ሙስና እንደየ ሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ፣ የሰው ልጅ ስልጣኔ እና ስርዓት በተለያየ መንገድ መጠንና አይነት የሚከሰት በመሆኑ አንድ ወጥና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ትርጉም ማግኘት ያስቸግራል፡፡ እንዲሁም ሙስና ሰው ሰራሽ ድርጊት/ወንጀል/ በመሆኑ ከሰው ልጆች ባህል፣ እሴት፣ የኣኗኗር ዘይቤ፣ የስልጣኔ ደረጃ… ወዘተ ጋር አብሮ የሚለወጥና የሚቀያየር በመሆኑ ወጥ ሆነ ትርጉም ለመስጠት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ለምሳሌ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ጉቦ የሚቆጠር ድርጊት በሌላው ማህበረሰብ እንደ ስጦታ ሊቆጠር ይችላል፡፡ እንዲሁም አንድ የፖለቲካ አመራር ወይም ኃላፊ ለቤተሰቡ ለጓደኞቹ ለፓርቲ ደጋፊዎች ከሥራው ጋር በተያያዘ ድጋፍ ቢያደርግ በአንዳንድ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ትክክለኛ ተግባር ሲወሰድ በሌላው ማህበረሰብ የሙስና ወንጀል ይሆናል (World Bank 2006)፡፡ ከዚህ የተነሳ ብዙዎቻችን ስለ ሙስና ምንነት ግንዛቤ ቢኖረንም የሁላችንም ግንዛቤ ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል ማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው በመጀመሪያ ስለ ሙስና ምንነት መነጋገር የሚያስፈልገው፡፡ በመሆኑም በዚህ ትምህርት ውስጥ ለሙስና የተሰጡትን ትርጉሞች እንመለከታለን ::

**የስልጠናው ዓላማ:- ከዚህ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች:-**

1. የሙስና ትርጉምን ያብራራሉ
2. የሙስናን ልዩ ባህርያት ይዘረዝራሉ፣
3. የሙስናን ወንጀል ከሌሎች ወንጀሎች ጋር ያነጻጽራሉ:
4. የሙስና አይነቶችን ያብራራሉ፣ የሙስና መገለጫዎችን ይዘረ
5. የሙሰና መንስኤዎችን ይዘረዝራሉ፣ በመ/ቤታቸው ወይም በአካባቢያቸው ለሚታዩ ሙስናና ብልሹ አሰራር መንስኤዎችን ይለያሉ፣
6. ሙስና የሚያስከትላቸውን ዋና ዋና ጉዳቶች ያብራራሉ፣

## 1.1. ሙስና ምንድ ነው?

የሙስናን ትርጉምን ከማየታችን በፊት ሰልጣኞች ያላቸውን ግዛቤ ለመፈተሽ ከዚህ በታች የተሰጡትን መልመጃዎች እንሥራ፡-

**መልመጃ አንድ፡-** ሥር የቀረቡትን ተግባራት በሚገባ በማጤን ምን ምን ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች እንዳሉ በምክንያት በማስደገፍ ተወያዩባቸው፡፡

**ተግባር** 1. አቶ አቤል የተባለ ሾፌር መ/ቤቱ ለሚያሰራው ህንጻ የሚውል ብረት ከጂቡቲ ወደ ኢትዮጵያ እንዲያጓጉዝ ከተሰጠው የፌሮ ብረት ከ200 ሺህ ብር በላይ የሚያወጣውን ብረት ከፕሮጀክቱ ኃላፊና ንብረት ክፍሉ ጋር በመስማማት መንገድ በማራገፍ ሸጠው ገንዘቡን ለግላቸው ተከፋፈሉት፡፡

**ተግባር** 2. አንድ የመንግሰት የሥራ ኃላፊ የመሥሪያ ቤቱን መኪና እና ነዳጅ በመጠቀም ክፍለ ሀገር የሚገኙ ዘመዶቹን ለመጠየቅ ይሄድበታል እንዲሁም የግል ጉዳይ ለማከናወኛ ይጠቀምበታል፡፡

**ተግባር** 3. አንድ የመንግስት ሠራተኛ /የሥራ ኃላፊ/ የሥራ ሰዓት ሳያከበር እጅግ እየዘገየ መሥሪያ ቤቱ ይደርሳል፡፡ ቢሮውም ከገባ በኋላ በቀጥታ መደበኛ ሥራውን በመርመር ፈንታ ከሥራ ጋር ተያያዥነት በሌላቸው በተለያዩ ጉዳዮች ጊዜ ያሳልፋል፡፡ /ጋዜጣ ያገላብጣል፣ ኮምፒዩተር ጌም ይጫወታል፣ ኢ.ሜይል ቼክ ያደርጋል፣ ወዘተ/ ማታም አንድ ሰአት ያህል ቀድሞ ከቢሮው ወጥቶ ይሄዳል፡

**ተግባር** 4. የአንድ የመንግስት መ/ቤት ገንዘብ ያዥ በእጁ የገቡትን የተለያዩ የሂሳብ ሰነዶች ከፊትና ከኋላ ቁጥሮችን በመጨመር፣ በመሠረዝ፣ በመደለዝና በማጥፋት ብዙ ገንዘብ ለግል ጥቅሙ ማዋሉ በኦዲተር ተረጋገጠ፡፡

በመልመጃ አንድ ውስጥ የተመለከቱትን ተገቢ ያልሆኑ ተግባራትን ለያቻሁ? በመቀጠል ለሙስና ምንነት የተሰጡትን ትርጉሞች እንመልከት ::

“Corruption” የሚለው ቃል “Corruptus” ከሚለው የላቲን ቃል የተወሰደ ሲሆን ሙስና ደግሞ “Corruption” የሚለውን የእንግሊዝኛውን ቃል እንዲገልጽ የምንጠቀምበት ከግዕዝ የተወረሰ ቃል ነው፡፡

ትርጉሙም ማጥፋት፣ ማበላሸት፣ ህግን መጣስ …. ወዘተ ማለት ነው፡፡ በመስኩ ጥናትና ምርምር ያካሄዱ ምሁራን፣ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ ድርጅቶች የተለያዩ መገለጫዎችን መሠረት በማድረግ ሙስና ለሚለው ቃል የሰጧቸው ትርጉሞች በአገላለጽ የተለያዩ ቢሆኑም በይዘታቸው ግን ተቀራራቢ ናቸው፡፡

ለአብነት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ትርጉሞች እንመልከት፡-

1. ሙስና አደራን አለመጠበቅ፣ እምነትን ማጉደል ወይም አለመታመን፣በጉቦ፣ በምልጃና በአድሎ ሃቅን፣ ውሳኔን ወይም ፍትህን ማዛባት ነው (Transparency International 2008)፡፡

2. ሙስና ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም ሲባል ሥርዓቶችን፣ ህጎችን፣ ደንቦችን፣ አሰራሮችን፣ መርሆዎችን የመጣስ ማንኛውም ተግባር ነው (Kato, 1995)፡፡

3. ሙስና የመንግስትን ሥራ ሥነምግባራዊ እና ህጋዊ መሠረት ባለው መመሪያና ደንብ ላይ ተመርኩዞ ማከናወን አለመቻል ነው ይለዋል /የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ 1993/፡፡

4. ሙስና በግል ወይም በቡድን፣ በፖለቲካ መሪዎች ወይም በቢሮክራቶች ሥልጣንና ኃላፊነትን መከታ በማድረግ፣ የህዝብን ጥቅምና ፍላጐት ለግል ጥቅም የማዋል ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ድርጊት ሲሆን፣ በመንግስትና በህዝብ ሃብትና ንብረት ላይ ስርቆት መፈጸም፣ ዝርፊያ ማካሄድ፣ ማጭበርበር፣ ህግና ሥርዓትን ተከትሎ ከመሥራት ይልቅ በዝምድና፣ በትውውቅ፣ በፖለቲካ ወገንተኝነት፣ በጐሰኝነት፣ በኃይማኖት ትስስር ላይ ተመርኩዞ በመሥራት አድሎ መፈፀም፣ ፍትህን ማጓደልና ሥልጣንና ኃላፊነትን በህገወጥ መንገድ የጥቅም ማግኛ የማድረግ እኩይ ተግባር ነው /ኬምፔሮናልድና ሰርቦርዌል 2000/፡፡

5. ሙስና የፖለቲካና የመንግስት አስተዳደራዊ ኃላፊነትን ካለመወጣት የሚመነጭ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ሥርዓቶችን የመጣስ የሥነ-ምግባር ግድፈት ሲሆን ይህም ለግል ጥቅም ሲባል በህዝብ የተሰጠ ሥልጣንና ኃላፊነተን አላግባብ በመጠቀም ህግና ደንብ የመጣስ እኩይ ተግባራትን ያካትታል /ቻርለስ ሳን ፎርድ 1998/፡፡

6. ሙስና በመንግስትና በህዝብ የተሰጠን ስልጣንና ኃላፊነትን ለግል ጥቅም ወይም ሌላን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲባል አላግባብ መገልገል ነው (Kimberly, 1997, Klitgaard, 1990, vishny 1993 & stapen Horst, Ric, 1999) የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር የአማርኛ መዝገበ ቃላት /1993/፣ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ልማት ተበብር ድርጅት (OECD, Transparency International /2005/) ፡፡

ከላይ የቀረቡትን የሙስና ትርጉሞች ስናጤን ሙስና የሚለው ቃል በጣም ሰፊና ውስብስብ የሆኑ ኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራትን እና የወንጀል ድርጊቶችን አካቶ መያዙን መረዳት ይቻላል፡፡ በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተገለጹትን ትረጉሞች ስንመለከት የሙስና ወንጀል በግልም ይሁን በመንግስት ተቋማት ውስጥ ሊፈጸም የሚችል መሆኑን የሚያሳዩ ሲሆን በሌላ በኩል ከ3-6 የተዘረዘሩት ሙስና በመንግስት ተቋማት የሚፈጸም ህገወጥ ድርጊት መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ እነዚህ ድርጊቶች በግል ወይም በመንግስት ድርጅቶች ውስጥ የሚፈጸሙ ቢሆኑም አገሮች እንደሚያወጧቸው የፀረ-ሙስና ወንጀል ህጎች ትርጉሞቹ የተለያዩ መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ በሀገራችን ሁኔታ በሀገርሃብትና ሁለንተናዊ እድገት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ የበለጠ ትኩረት የተሰጠው በመንግስትና በህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ በሚፈጸም ሙስና ላይ ነው፡፡

ከላይ ለሙስና የተሰጡት ትርጉሞች ስንመለከት በአጭሩ ሙስና ህግና ሥርአትን ተከትሎ ከመሰራት ይልቅ ስልጣንና ኃላፊነትን መከታ በማድረግ ህግና ሥርአትን በመጣስ የመንግስትና የህዝብ ሃብትና ንብረትን በመስረቅ፣ በመዝረፍ፣ በማጭበርበር እንዲሁም በጉቦ፣ በዝምድና፣ በትውውቅ፣ በጎሰኝነት፣ በፖለቲካ ወገንተኝነትና በኃይማኖት ትስስር ላይ በመመርኮዝ አድሏዊ በሆነ አሰራር ፍትህን እያዛቡ የግል ጥቅምን ማካበትና ሌላን ወገን ተገቢ ባልሆነ መንገድ መጥቀም ወይም ሙጉዳት እንደሆነ ከተሰጡት ትርጓሜዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 1.2. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያትን ከሚከሰትበት ሁኔታ እና ከሌሎች ወንጀሎች ጋር በማነጻጸር በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል:: ሰልጣኞች እነዚህን ባህርያት በዝርዝር ከማየታችሁ በፊት ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን መልመጃ ሥሩ::

**መልመጃ ሁለት፡-** በቡድን በመሆን በሚከተሉት ሃሳቦች ላይ ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡ ሙስና ከሚከሰትበት ሁኔታ አንጻር፡-

1. በተለያዩ ዘርፎች የሚከሰት (Melti-Sectoral) ነው፣
2. በተለያዩ የ ላፊነት ደረጃዎች በሚገኙ ሰዎችና በሌሎች/የመንግስት ሠራተኞች ባልሆኑ ግለሰቦች (MeltiLevel) የሚፈጸም ነው፣
3. በተለያዩ መንገዶች የሚከሰት (Manifasted in many ways) ነው፡፡ እንዴት? በምሳሌ አስረዱ፡፡

የተለያዩ ጥናቶችና ልምዶች እንደሚያመለክቱት ሙስና ከሚከሰትበት ሁኔታ እና አፈጻጸም ከሌሎች ወንጀሎች ጋር ሲነጻጸር የሚከተሉት **ባህርያት አሉት፡-**

**1. ከሚከሰትበት ሁኔታ አንጻር**

ሀ. በተለያዩ ዘርፎች የሚከሰት (Multi Sectoral) መሆኑ ሙስና በተለያዩ ሴክተሮች የሚፈጸም የመልካም አስተዳደርና የኢኮኖሚ ችግር ሲሆን ይሄም በልማት እና በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል፡፡ በውጤቱም የብልሹ አስተዳደር ደካማ የኢኮኖሚ ስርአት እንዲሁም አዝጋሚ የሆነ የልማት እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡

ለ. በተለያዩ ደረጃዎች በሚገኙ ሰዎች የሚፈጸም (Multi-level) መሆኑ ይህ የሚያመለክተው በተለያዩ የመንግስት መዋቅር ወይም ከቀበሌ አስከ ማእከል፣ በተለያዩ እርከኖች ላይበሚገኙ አንዳንድ ኃላፊዎች፣ ባለስልጣናት፣ ሠራተኞች እና ሌሎች ግለሰቦች በሚሳተፉበት ሁኔታ የሚፈጸም መሆኑን ነው፡፡

ሐ. በብዙ አይነት የሚገለጽ (Manifaseted in Many Ways) መሆኑ ሙስና በከፍተኛ(grand)፣ ወይም በዝቅተኛ (petty)፣ ተቋማዊ (institutional)፣ በግለሰብ ደረጃ (individual)፣ ግለሰቦች ተደራጅተው (organized) እንዲሁም ሳይደራጁ (disorganized) በተለያየ መንገድ እና መጠን የሚፈጸም መሆኑን ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል የሙስና ወንጀል በአፈጻጸሙ ከሌሎች ወንጀሎች ጋር ሲነጻጸር የተለዩና ውስብስብ ባህርያት አሉት:: እነዚህን ባህርያት በተመለከተ ቀጥሎ የቀረበውን መልመጃ ሥሩ:-

**መልመጃ ሦስት መመሪያ:-**

በቡድን በመሆን ኬዝ አንድን መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ሃሳቦች ላይ ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

**የሙስና ወንጀል በአፈጻጸሙ ከሌሎች ወንጀሎች አንጻር ሲታይ የተለየና ውሰብስብ የሚያደርጉት ባህርያት አሉት:: እነዚህም-፡**

1. **የአፈፃፀሙ ሂደትና ሥልት ውስብስብ መሆን፣**
2. **በአብዛኛው ለጉዳዩ ባለቤት ነኝ ባይ አለመኖር፣**
3. **የፈፃሚዎቹ ማንነት፣**
4. **በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደ ነውር አለመታየቱና ሙስናን በመዋጋት ተግባር ላይ የተሠማሩትን ማሸማቀቁ ነው::** እንዴት? ቀጥሎ የቀረበውን ኬዝ አንድን በጥሞና በመረዳት እነዚህ ኬዝ አንድ በአንድ ወቅት አንድ ትልቅ አስመጪ የንግድ ድርጅት በርካታ መጠን ያላቸውን ሸቀጦች በ16 ዲክላራሲዮኖች አማካኝነት ዲክለር አስደርጎ ወደ ሃገር ውስጥ ያስገባል፡፡ ይሁንና አስመጪዎቹ እቃዎቻቸውን ከጉምሩክ ሲያስወጡ መንግስት ከሚጠብቅባቸው 13,457,694ብር (አስራ ሦስት ሚሊዮን አራት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና አራት ብር) ከሚጠጋ የታክስና የቀረጥ ክፍያ ውስጥ ምንም ገቢ አላደረጉም፡፡

   ለዚህ ድርጊታቸው የኮምፒዩተር ክፍል የአሲኩዳ ሲስተም ሠራተኞችን፣ ሌሎች የጉምሩክ ሰራተኞችን፣ አስመጪ እና የወጪና ገቢ ንግድ አስተላላፊዎችን በመጠቀምና በመደለል ከጀርባቸው አሰልፈዋል፡፡ የድርጊታቸው ተባባሪ ከሆኑ የጉምሩክ ባለስልጣን የኮምፒዩተር ባለሞያዎች ጋር በመመሳጠር የዲክላራሲዮኖቹን ሙሉ መረጃ ከኮምፒዩተር አሲኩዳ ሲስተም ማስወገድ የቻሉ ሲሆን፣ በሌሎች ሰራተኞች አማካኝነት ደግሞ ሌሎች አባሪ ሰነዶች/ሃርድ ኮፒ/ ማስረጃዎች እንዲሰወሩ አድርገዋል፡፡

በተጨማሪም ይህን ወንጀል ለማጋለጥ ቁልፍ የሆነ መረጃ ያለውን ሰው ለማጥፋት ጥረት አድርገዋል። ይህ ሰው በተጠርጣሪዎች አማካኝነት በስሙ የንግድ ፈቃድ የተከፈተለትና በመጋዘን ጠባቂነት እንዲሰራ በ700 ብር የቀጠሩት ሰው ነው። በግለሰቡ ስም ንግድ ፍቃድ እንዲወጣ ቢደረግም በንግድ ፈቃዱ የሚጠቀመው በውክልና የተሰጠው ሌላ ሰው ነበር። በዚህ ሰው ስም በርካታ መጭበርበሮች የተፈጸሙ ሲሆን በ16 ዲክላራሲዮኖች ዲክለር ተደርገው በህገወጥ መንገድ እንዲገቡ ከተደረጉእቃዎች ውስጥ 3 ዲክላራሲዮኖች በግለሰቡ ስምተገኝተዋል። ስለሆነም ይህን ሰው (የመረጃ ምንጭ) ቢቻል መረጃ እንዳይሰጥ ማድረግ ወይም እንዲክድ አሊያም ከፌደራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንም ሆነ ከሌላ የሚመለከተው የህግ አካል ማራቅና ከእይታ ውጭ ማድረግ ይገባቸው ነበር። በመጨረሻም ግለሰቡ መረጃ ከመስጠት ወደ ኋላ እንደማይል ሲገነዘቡ ሰውየውን ከእይታ ለማራቅና ወንጀሉን ለማዳፈን ሞክረዋል።

ለዚህ ተግባራቸው ደግሞ ግለሰቡ ከ11ዓመት በፊት በሶማሌ ክልል በሽንሌ ከተማ ፈጽሞታል የተባለ ወንጀልን ቀስቅሶ እንዲከሰስና ከአዲስ አበባ ታፍኖ እንዲወሰድ ማድረግ ብቸኛ አማራጭ ሆኖ አግኝተውታል። በመሆኑም ተጠርጣሪዎች ለእኩይ ተግባራቸው ተባባሪ ከሆኑ ምግባረ ብልሹ ዳኞች እና ፖሊሶችጋር በመሻረክ ይህ ሰው ከአዲስ አበባ ወደ ሽንሌ ተወስዶ ክስ እንዲመሰረትበት ካደረጉ በኋላ በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ከማንም ሰው ጋር እዳይገናኝ ተዘግቶበት በቂ ምግብና ውሃ ሳያገኝ ለአንድ ወር ያህል እንዲታሰር ማድረግ ችለዋል።

## 2. አፈጻጸሙ ከሌሎች ወንጀሎች አንጻር ሲታይ

### ሀ . የአፈጻጸሙ ሂደትና ስልት ውስብስብ መሆን

እንደ ግድያ እና ሌሎች የተለመዱ ወንጀሎች በስሜታዊነት ወይም በግብታዊነት የሚፈጸሙ ናቸው። ብዙ ጊዜ ከጥላቻ፣ ከቂም በቀል፣ ጊዜያዊ ፍላጎትን ከማርካት፣ ዕለታዊ ችግርን ከመቅረፍ፣ ከዝሙት ፍላጎት ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ናቸው። እነዚህ ወንጀሎች አብዛኛውን ጊዜ የአፈጻጸማቸውን ሂደትና ስልት ድብቅ ለማድረግ በማለም በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈጸሙ ሳይሆን በስሜታዊነት፣ በግብታዊነትና በጀብደኝነት የሚፈጸሙ ናቸው።

ስለዚህ እነዚህን የመሳሰሉ ወንጀሎች ሲፈጸሙ የሚተውት አሻራና መረጃ ይኖራል፤ ለምሳሌ ሰው ተገድሎ ከሆነ ወንጀሉ የተፈጸመበት መሣሪያው /ቀለሃ፣ ቢላዋ፣ ዱላ፣ ወዘተ/ ወይንም አሻራው ይገኛል፡፡ በዚህም ወንጀሉን ማን እንደፈጸመው ለማወቅ መነሻ የሚሆን መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተቃራኒ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው በስሜታዊነት፣ በግብታዊነትና በጀብደኝነት ሳይሆን የአፈጻጸሙን ሂደትና ሥልት እንዳይደረስበት ለማድረግ በከፍተኛ ጥናት፣ በጥንቃቄና በሚስጢር የሚፈጸም ነው፡፡ ስለዚህ ወንጀሉ ስለመፈጸሙ የሚጠቁም መረጃ ለማግኘት አዳጋች በመሆኑ ከሌሎች ከተለመዱ ወንጀሎች የተለየና ውስብስብ ያደርገዋል፡፡

**ለ. ለጉዳዩ ባለቤት ነኝ ባይ አለመኖር**

ግድያ እና ሌሎች የተለመዱ ወንጀሎች የሚያደርሱት ጉዳት በአንድ ቤተሰብ ወይንም ግለሰብ ላይ በቀጥታ የሚታይ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተበዳዩ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በደሉን ለህግ ቶሎ የሚያቀርብበት ሁኔታ አለ፡፡

ከዚህ በተቃራኒው የሙስና ወንጀል የሚያደርሰው ጉዳት በአንድ ወይም በተወሰነ ቤተሰብና ግለሰብላይ የሚወሰንና በቀጥታ የሚታይ ሳይሆን አገርንና ህዝብን በሙሉ የሚያጠቃልል መጠነ ሰፊ ነው፡፡

ይሁንና የሙስና  ወንጀል ሲፈጸም የተፈጸመውን ወንጀል የማጋለጥ ወይም የመታገልሃገራዊ ግዴታ አለብኝ፣ እንደ ዜጋ ይመለከተኛል በማለት ጉዳዩን ለህግ የሚያቀርብ ሰው በጣም ጥቂት ነው፡፡ የሙስና ወንጀልን የራሴ ጉዳይ ነው ወይም ለጉዳዩ ባለቤት ነኝ በማለት ለህግ የሚያቀርብና ማስረጃ በማቅረብ የሚተባበር ሰው ማግኘት /ከሌሎች ወንጀሎች ጋር ሲነጻጸር/ አስቸጋሪ በመሆኑ ወንጀሉን ከሌሎች የተለመዱ ወንጀሎች ልዩ፣ ውሰብስብና ድብቅ ባህሪ እንዲላበስ ያደርገዋል፡፡

**ሐ.** የፈፃሚዎቹ ማንነትና ምርመራውን የማደናቀፍ ወይም ፍሬቢስ የማድረግ ጥረት ግድያ እና ሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር የሚባሉ ወንጀሎች በአብዛኛው የሚፈጸሙት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃላይ በሚገኙና በትምህርትም ብዙ ባልገፉ ሰዎች ሲሆን በሌላ በኩል በተለይ ከፍ ያለ የሙስና ተግባር የሚፈጸመው በኑሮ ደረጃቸው /የተሻሉ/ ከፍተኛ እውቀት፣ ሥልጣንና ገንዘብ ባላቸው ሰዎች ነው፡፡

ስለዚህ የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት ሰዎች አስቀድሞ በተጠናና በረቀቀ ዘዴ በተቀነባበረ መንገድ ራሳቸውን አደራጅተው፣ ስልቶችን በጥንቃቄነድፈው፣ ከተጠያቂነት ማምለጥ የሚችሉበትን መንገድ ሁሉ ቀድመው አመቻችተው በመሆኑ ወንጀሉን የተለየ ውስብስብና ረቂቅ ባህሪ እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሙስና ፈጻሚዎቹ የመወሰን አቅምና ሥልጣን ስላላቸው ምርመራ እንዳይካሄድ በማደናቀፍ ሂደቱን እንዲዘገይ የማድረግ፤ ምርመራው ቢካሄድም ልፍስፍስ እንዲሆን

በማድረግ የተጠርጣሪዎችን የተጠያቂነት ደረጃ ማሳነስ ወይም ነጻ እንዲወጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ የተጀመረን ምርመራም እንዲኮላሽ ማድረግ ሲሳናቸው ደግሞ መርማሪውንም ሆነ

ከምርመራው ጋር ግንኙት ያላቸውን ግለሰቦች በተለያየ መንገድ ማጥቃት ወይም ማስጠቃት፣ ከዚህ በተጨማሪ ሙስናን የሚመረምረውንና የሚከሰውን አካል እራሱ በሙስና እንዲዘፈቅ በማድረግ ወንጀሉን የመከታተልና የማጋለጥ ሥራ የተለየ፣ ውስብስብና ረቂቅ ባህርይ ያላብሰዋል፡፡

**መ.** በአብዛኛው ሰዎች ዘንድ እንደ ነውር አለመታየቱ ሰዎች ግድያ እና ሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር የሚባሉ ወንጀሎች መፈጸማቸውን ሲያዩም ሆነ ሲሰሙ ሲዘገንናቸውና ሲያወግዙ በግልጽ ይስተዋላል፡፡ በድብቅ ወንጀሎችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ህዝቡ ባህላዊና ሥነልቦናዊ ተጽእኖ በማሳደር የወንጀሉ ፈጻሚዎች በባህላዊው ወይም በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርበው ተገቢ ቅጣት እንዲያገኙ ፍላጎቱ በመሆኑ የተለያዩ ባህላዊ የወንጀል ማወጣጫ ዘዴዎችን ሲጠቀም ይስተዋላል፡፡

ነገር ግን ሙስናን በሚመለከት ሰዎች እንደሌላው ወንጀል የማያነውሩት መሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜም ሙስና የፈጸመ ሰው እንደብልጥና ቀልጣፋ ሲደነቅ ይስተዋላል፡፡ "የሺን ገንዘብ ብላው የሺን ወንድም ፍራው፣ ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል፣ ወዘተ…" ምሳሌያዊ አባባሎች ሙስናን እንደ ነውር ሳይሆን እንደብልጥነት፣ በመንግስት አስተዳደር ውስጥ ተቀጥሮ ቅንና ቀና መሆን እንደሞኝነት የሚታይ እንደሆነ የሚያመለክቱና ሙስናን የሚያበረታቱ አባባሎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ህብረተሰቡ የማያነውረው ተግባር ላይ ማስረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ይህም ሙስናን በመዋጋት ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚደርስባቸው ጥላቻና ውግዘት ከሚፈጥርባቸው የሥነልቦና ጫና የተነሳ ስለሚሸማቀቁ ለፍርድ ሂደቱ አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን እንዳያገኙ እንቅፋት ይሆንባቸዋል፡፡ ይሄም የሙስና ወንጀል የተለየ ባህርይ እንዲላበስ አስተዋጽ ኦያደርጋል፡፡

ይሁን እንጂ በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደ ነውር ያለመታየቱ ችግር ቢኖርም እንኳ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ኅብረተሰቡ የሙስና ወንጀል ስለሚያስከትለው ጉዳት ግንዛቤው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ ድርጊቱ ሰለመፈጸሙ ጥቆማ የሚያቀርቡ ዜጎች ቁጥር መጨመሩን የፌዴራልና የክልል የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች አመታዊ ሪፖርቶች ያረጋግጣሉ::

## 1.3. የሙስና ዓይነቶችና መገለጫዎች

የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሙስና ከአፈፃፀሙ፣ ከፈፃሚዎች ማንነት፣ ከሚያስከትለው ጉዳትና ከሚፈፀምበት አካባቢ አንፃር በተለለያየ መልኩ ሊከፈል ይችላል፡፡ ከሚፈጸምበት አካባቢና ከሚያስከትለው ጉዳት በመለሳትዝቅተኛ ሙስና (Petty Corruption)፣ ከፍተኛ ሙስና (Grand Corruption) እና ፖለቲካዊ ሙስና (Political Corruption) ብለን ልንከፍለው እንችላለን፡፡ የሙስና መገለጫዎችንም በተመለከተ ብዙ ሰዎች በተለይ ቀድም ባሉት ጊዜያት ሙስና የሚለውን ቃል ሲሰሙ በመጀመሪያ ወደ አዕምሮአቸው የሚመጣው ጉቦ/እጅ መንሻ/ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን ባለንበት ዲጅታል ዓለም ከዚህውጪ በርካታ የሙስና መገለጫዎች እና የሙሰና አይነቶች አሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ትምህርት ውስጥ ስለሙስና አይነቶች እና ስለሙስና መገለጫዎች የምንመለከትበት ይሆናል::

## 1. የሙስና አይነቶች

### ሀ/ ዝቅተኛ ሙስና (Petty Corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ መጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡

ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን፣ በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡ ዝቅተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ አንድ ጊዜ ተፈጽሞ የማያበቃ፣ በዕለት ተዕለት ህይወት በመንግስትና በህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ የሚከሰት ነው፡፡ አገልግሎት ለማግኘት በሚኬድባቸው የመንግስትና የህዝብ ተቋማት ውስጥ አገልግሎት ፈላጊው ማግኘት የሚገባውን አገልግሎት በመከልከል ወይም አገልግሎት ፈላጊው የማይገባ አገልግሎት በሚጠይቅበት ጊዜ በየደረጃው ያሉ አንዳንድ

ቢሮክራቶች በቀላሉ ሊፈጽሙት የሚችሉት በመሆኑ ቶሎ የሚሰማ እና አብዛኛውን ህዝብ የሚያማርር ነው።

ይሁ

ዝቅተኛ ሙስና ስሙ እንደሚያመለክተው ዝቅተኛ ሳይሆን የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡ የዝቅተኛ ሙስና መገለጫ መንገዶች እና ተግባራትዝቅተኛ ሙስና (Petty corruption) የሚፈፀመው የተለመዱ መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ህጋዊ አሰራሮችን በመጣስ ሲሆን በዋነኛነት በጉቦ፣ በስርቆት እና በማጭበርበር ይገለፃል፡፡

ለአብነት ያህል እነዚህ መገለጫዎች በሚከተሉት ተግባራት ውስጥ እንደሚከሰቱ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡

- በመንግስትና በህዝብ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ጉቦ መቀበል፣
- ፍተሻ ጣቢያ ላይ ጉቦ በመቀበል ህገወጥ ዕቃዎችን ማሳለፍ፣
- የግብር ምደባን በጉቦ እና በመደለያ በመስራት ያልተመጣጠነ የገቢ ግብር ምደባ ማካሄድ፣
- በልዩ ልዩ የቢሮ መሳሪያዎች እና በተሽከርካሪ ግዥ እና ጥገና ወቅት በሚደረግ ማጭበርበር /ሰነዶችን በመሰረዝና በመደለዝ/
- በልዩ ልዩ የወጪ እና ገቢ ሰነዶች ላይ ማጭበርበር /ሰነዶችን በመሰረዝ፣ በመደለዝ እና በማጥፋት/፣
- በልዩ ልዩ የግንባታ የጥገና እና የአገልግሎት ጨረታዎች የማጭበርበር ተግባር በመፈፀም፣
- ህገወጥ የትምህርት እና የህክምና ማስረጃ በመስጠት ወይም በትምህርት ወይም በስልጠና የተገኘን ሙያ ህገወጥ በሆነ መንገድ /ህዝብን ሊጎዳ በሚችል መልኩ/ በመጠቀም የሚፈጸም ነው፡፡

**ለ/ ከፍተኛ ሙስና (Grand Corruption)**

ይህ የሙስና አይነት መጠኑ ሰፊ የሆነ የህዝብና የመንግስት ሀብት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚመዘበርበትና የሚዘረፍበት የሙስና ወንጀል ሲሆን በአፈጻጸሙም ከፍተኛ

የመንግስለባልስጣናት፣ ከፍተኛ  የፖለቲካ አመራር አካላት እና ሀብትና ዕውቀት ያላቸው ግለሰቦች የሚሳተፉበት ነው፡፡

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ  ስልት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ፈጻሚዎቹ ከፍተኛ ስልጣን፣ እውቀትና ሃብት ያላቸው በመሆናቸው ድርጊቱን በረቀቀ ስልት የመፈጸምና ሚስጢራዊ የማድረግ አቅሙ ስላላቸውነው፡፡

በ1997ዓ.ም. ተሻሽሎ በወጣው የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/9/ መሠረት ከባድ /ከፍተኛ/የሙስና ወንጀል የሚባሉት ከዝቅተኛ የሙስና ወንጀል

**የሚለዩባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡-**

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያካተቱ የሙስና ወንጀሎች /ለምሳሌ የገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶች፣ ባንኮች፣ በመሠረተ ልማት ግንባታ ላይ የተሰማሩ መሥሪያ ቤቶች፣ ፖሊስ፣ የደህንነትና የመከላከያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ወዘተ/ ወይም፣

ለ. የመንግሥት ባለሥልጣናትን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች  /በምርመራ  ሂደትም  ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቁ፣ በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መልኩ የሚያስከትሉት ውጤት ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ሲሆን ወይም፣

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፣  ኢኮኖሚ፣  ጸጥታ  እንዲሁም  በሕብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ ሚችሉ የሙስና ወንጀሎች በከፍተኛ  መስና ደረጃ  የሚፈረጁና ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸውናቸው፡፡

**የከፍተኛ ሙስና መገለጫ መንገዶች**

ከፍተኛ ሙስና (Grand Corruption) በዋነኛነት በጉቦ፣ በማጭበርበርና በዝርፊያ የሚገለጽ ሲሆን ለአብነት ያህል እነዚህ መገለጫዎች በሚከተሉት ተግባራት ይከሰታሉ፡-

- በአገር ደረጃ በሚከናወኑ የጦር መሳሪያዎች ላይ በሚፈጸም ህገወጥ ግዥ /እንደጦር አውሮፕላኖች፣ ታንኮች መርከብ እና ልዩ ልዩ ከባድ መሳሪያዎች በመሳሰሉት/፣

- ህገወጥ በሆኑ ጨረታዎች በሚፈጸሙ ከፍተኛ የግንባታ ውሎች /ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግንባታዎች፣ ከፍተኛ የመስኖ እና የመጠጥ ውሃ ግድብ ግንባታዎች፣የመንገድ ሥራዎች፣ በከባድ ፋብሪካዎች ግንባታዎች /

- ልዩ ልዩ ለአገር ውስጥ ምርት አገልግሎት የሚውሉ እንደማዳበሪያ፣ ኬሚካሎች፣ መድሐኒቶች፣

- የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች እና የትምህርት መገልገያ መሳሪያዎች ለመግዛት በሚፈጸሙ ህገወጥ ግዥዎች፣

- ከፍተኛ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦቶች ላይ በሚፈጸም ህገወጥግዥዎች እና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

### ሐ/ ፖለቲካዊ ሙስና (Political corruption)

ፖለቲካዊ ሙስና በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጉልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Coruption) ፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡

ሀ. በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ በብዙ አገሮች የፖለቲካ መሪዎችና ፓርቲዎች ሙስና ውስጥ የሚገቡት ስልጣን ለመያዝ ወይም በስልጣን ላይ

ለመቆየት ካላቸው ፍላጐት የተነሳ ነው፡፡ ይህን ፍላጎታቸውን ለማሳካት በምርጫዎች ለማሸነፍ የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ፡፡ በምርጫ ሂደት የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎች፡

- በምርጫ ወቅት የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ሥራ ለመሥራት በመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም ላይ ኢ-ፍትሃዊና አድሎአዊ አሰራር በመፈጸም ህዝቡ አማራጭ እንዳይኖረው መገደብ፣
- በምርጫ ወቅት ለመራጮች ገንዘብ ወይም ልዩ ልዩ መደለያ በመስጠት ምርጫቸውን ማስቀየር፣
- በምርጫ ወቅት ለተመራጮች ገንዘብ ወይም ልዩ ልዩ መደለያ በመስጠት እንዳይወዳደሩ ማድረግ፣ ወይም በህግ አውጪው በኩል የሚጠቅማቸው ህግ እንዲወጣ ወይም ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ለማድረግና ለተመራጮች የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ በፋይናንስ መደገፍን ያካትታል፡፡

ለ. የሲቪል ሰርቪሱን መዋቅር ለፖለቲካ ጥቅም ፍላጐት ማሟያ ማዋል ይህ ለፓርቲውና ለፖለቲካው ታማኝና ደጋፊ ለሆኑ ሰዎች የተለየ ጥቅምና ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ሲባል እውቀትንና ችሎታን መሰረት ባደረገ ውድድር ከማስያዝ ይልቅ ለፓርቲውና ለፖለቲካው ታማኝ ከመሆን አንፃር የሲቪል ሰርቪሱን መዋቅር በመሙላት የሚፈጸም ፖለቲካዊ ወገንተኝነትን የሚመለከት ነው፡፡

በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ የሚሰጥ ኃላፊነት ለፖለቲካው ታማኝ በመሆን ላይ የተመሠረተ ከሆነ ተቀጣሪዎች ታማኝነታቸውን ለማሳየትና ደረጃቸውን ለማሳደግ የፖለቲካ ጥቅም በማስጠበቅ ሥራ ላይ ይጠመዳሉ፡፡ የዚህ ድምር ውጤትም አስተዳደራዊ ሥራዎች ከፖርቲ አሰራር አንጻር እንዲቃኙ ምክንያት ይሆናል፡፡

የመንግስትና የፓርቲ ሥራ ይቀላቀላል፤ የደረጃ እድገትና የደሞዝ ጭማሪ የፖለቲካ ወገንተኝነትን መሠረት እንዲያደርግ ያስገድዳል፤ ይህ ደግሞ የሥራ ተነሳሽነት እንዲቀን ስያደርጋል፡፡

ሐ. ሕግ በማውጣት ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና የተወሰኑ ወገኖችን ጥቅም ለማስጠበቅና ለመርዳት በሚመች መልኩ ህግ እንዲወጣ ደንብና ፖሊሲ እንዲቀረጽ ተጽዕኖ ለማድረግ ወይም በፖሊሲ ቀረፃ ወቅት የወከሏቸው ቡድኖች የግልና የቡድን ፍላጐታቸውን በህግ፣ በደንብና በፖሊሲ ውስጥ እንዲያካትቱ ለመንግስት ባለሥልጣናት፣ ለፖለቲካ አመራር አባላትና ለህዝብ ተመራጮች ከፍተኛ ገንዘብ በመስጠት፣ በማግባባትና ተጽእኖ በማሳደር የሚፈጸም ወንጀልን የሚመለከት ይሆናል፡፡ ከዚህ በታች የተገለጹ ኬዞችን መነሻ በማድረግ መልመጃውን ሥሩ::

**መልመጃ አራት:- መመሪያ**

1. ከታች የተገለጹትን ኬዞች በመመርመር የተፈፀሙ ሙስናዎችን እና የሙስና መገለጫዎችን ለዩአቸው፡፡

   **ኬዝ አንድ**

በአንድ የመንግስት መገናኛ ብዙኃን ድርጅት ውስጥ በተለያዩ ኃላፊነት ላይ የነበሩ ሁለት ጋዜጠኞች ከድርጅቱ የተረከቧቸውን የተለያዩ የኦዲዮ እና የኦዲዮ ቪዥዋል መረጃዎችን ከድርጅቱ እውቅና እና ፍቃድ ውጪ የድርጅቱን የኦዲዮ እና የኦዲዮ ቪዥዋል ላይብራሪ አጠቃቀም መመሪያና የኢዲቶሪያል ፖሊሲን በመጣስ ለአንድ የውጪ የግል ቴሌቪዥን ድርጅት አሳልፈው በመስጠታቸው ህግ ፊት ቀርበው የቅጣት ውሳኔተላለፈባቸው።

**ኬዝ ሁለት**

በኢትዮጵያ ዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ስር በሚተዳደረው የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፈንድ መ/ቤት ውስጥ የጨረታ ኮሚቴ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሰራ የነበረ አንድ ግለሰብ ነበር። በአንድ ወቅት ከዓለም ባንክ በዕርዳታ በተገኘ 130 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የገጠር ኤሌክትሪክ ማስፋፊያዎችን ለማሰራት ዓለም አቀፍ ጨረታ ይወጣል።

ታዲያ በዚህ ጊዜ ይኸው ግለሰብ ከጨረታው ጋር በተያያዘ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችጋር ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ማድረግ ይጀምራል። በዚህ ሁኔታ ግለሰቡ OMNI Agricultural Ltd, Israel ከተባለና በጨረታ ለመወዳደር ካመለከተ የእስራኤል ኩባንያ ጋር በስልክና በኢ-ሜይል በመገናኘት 5,000.00 የአሜሪካን ዶላር እንዲሰጡት ይጠይቃል፤ በቀጣይም Solener Madrid, Spain ከተባለ የስፔን ጨረታ ተሳታፊ ኩባንያ ጋር በተመሳሳይ መንገድ ግንኙነት በማድረግ 450.00 ዩሮ በዌስተርን ዩኒየን በኩል ይቀበላል። እንዲሁም Anjelique International Ltd. ከተባለ የህንድ ኩባንያ ጋር ባደረገው ግንኙነት ጨረታው ሳይከፈት የኩባንያውን የጨረታ ሰነድ በግሉ በሚስጥር መርምሮ እንዲያስተካክሉ ሃሳብ ሰጥቷቸዋል። በተጨማሪም የኮሚዩኒኬሽንና አክሰሰሪዎች ኢንተርናሽናል ጀርመኒ (ሲ.ኤ.ኤ) ከተባለ ኩባንያና የኩባንያው ዳይሬክተር

ከሆኑት ግለሰብ ጋር ግንኙነት በማድረግ በዌስተርን ዩኒየን በኩል 4,250.00 የአሜርካን ዶላርይቀበላል፡፡

እንዲሁም ከአንድ ጀርመናዊ ግለሰብ ጋር የኢ-ሜይል ግንኙነት በመፍጠር «በጨረታው ዝርዝር ውስጥ አስገባዎታለሁ» በሚል 725 የአሜርካን ዶላር እንዲላክለት ጠይቋል፡፡ ባጠቃላይ ግለሰቡ በድምሩ 10,684.00 ያህል የአሜሪካን ዶላር ከተለያዩ ኩባንያዎች ጠይቋል፤ ከፊሉን ደግሞ ተቀብሏል፡፡ በሌላ በኩል ግለሰቡ ምንጩ ያልታወቀ በድምሩ ብር 827,000 ይዞተገኝቷል፡፡

**ኬዝ ሦስት**

በአንድ ክ/ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት አቃቤህግ የነበረ አንድ ግለሰብ በክፍለ ከተማው ፍትህጽ/ቤት ከግብርጋር በተያያዘ ክሱ በሂደት ላይ ያለን ግለሰብ ጉዳዩን ለመዝጋት ብር50000 (ሃምሳሺህ) ሲቀበል እጅ ከፍንጅ ተያዘ፡፡

**2. የሙስና መገለጫዎች**

ሙስና በዓይነት እንደሚለያይ ሁሉ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና መንግስታዊ በሆኑ ድርጅቶች ውስጥም በተለያዩ ድርጊቶች የሚገለጥ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩትን ዋና ዋና የሙስና መገለጫዎች እንመልከት፡-

1. **ጉቦ**

ጉቦ አንድን ኃላፊ ወይም የመወሰን ሥልጣን ያለው ሠራተኛ ተግባሩን ወይም በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ በማከናወን ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ሲገባው የተሰጠውን ኃላፊነት ተገቢ ያልሆነ ጥቀም ለማግኘት ወይም አንድን ኃላፊ ወይም የመወሰን ሥልጣን ያለው ሠራተኛ ተግባሩን ወይም በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዳያከናውን ሐሳቡን ወይም ድርጊቱን ለማስለወጥ ወይም በኃላፊነቱ ማድረግ የሚገባውን ትክክለኛ ተግባር

እንዳይፈጽም ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲፈጽም ለማድረግ የሚሰጥ ወይም የሚጠየቅ ተግባር ነው፡፡ አንድን ወይም ከአንድ የበለጡ ግለሰቦችን በማባበልና መደለያ በመስጠት ሕጋዊ አሠራርን በማስለወጥ ወይም በመለወጥ ሕገወጥ ጥቅም ለማግኘት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም ጉቦን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡

- ከአገልግሎት ፈላጊ የሚመነጭ ጉቦ (Bribery)- ይሄኛው የጉቦ ዓይነት ከአገልግሎት ተቀባይ /ከተገልጋይ/ የሚነሳ ሲሆን ለአገልግሎት ሰጪው መደለያ በመስጠት ሕጋዊ አሠራርን ለማስለወጥ የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ ይኸውም፡-

ሀ. ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣ በቀላሉ የማይገኙ ነገሮችን ለማግኘት ወይም ከክፍያ ነፃ ለመሆን/የገቢና የወጪ ንግድ ፈቃድ ለማግኘት፣ በውጭ ምንዛሪ መንግስት የሚያወጣቸውን ጨረታዎች ለማሸነፍ፣በመሬት ድልድል … ወዘተ/፣

ለ. ከሕጋዊ ክፍያ ነፃ ለመሆን፣ ታክስና የጉምሩክ ቀረጥ ለማስቀነስ፣ የዋጋ ቁጥጥር እንዳይኖር ለማድረግ፣ ወዘተ

ሐ. ፈጣን አገልግሎት ለማግኘት ወይም መረጃ ለማግኘት /የጨረታ መረጃዎች፣ የፍትህ አካላትን ውሳኔ/፣

መ. አንድን ጥቅም ሌሎች እንዳይካፈሉና ለብቻ ለመጠቀም የሚከፈል /ተወዳዳሪዎችን ከገበያ ለማስወጣት/፡፡

- ከአገልግሎት ሰጭ የሚመነጭ ጉቦ (Extortion or Extraction)- ይህኛው የጉቦ ዓይነት መሰጠት የሚገባውን ህጋዊ አገልግሎት በመከልከል ከአገልጋይ የሚጠየቅ ሲሆን ተገልጋዩን በማስፈራራት፣ በማስጨነቅ፣ ተጽእኖ በማሳደር ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ተግባርነው፡፡ የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች፡-

- ግለሰቦችን ወይም ድርጅቶችን ከሚደርስባችሁ ጥቃት እንጠብቃችኋለን በማለት፣

- አስቀድሞ ግለሰቦቹ ወይም ድርጅቶቹ የሚያስፈራቸውን ሁኔታ በመፍጠርና ይህንን የተፈጠረውን ሁኔታ እከላከላለሁ ወይም አጠፋለሁ ብሎ በመቅረብ፣

- በግለሰቦችና በድርጅቶች ላይ በስውርና በተቀነባበረ መንገድ የተጋነነ የግብርና የታክስ ተመን እንዲጣልባቸው በማድረግና ያንን እንደሚያስቀንሱ ሆነው በመቅረብ፣

- የፈቃድ ጥያቄዎች (licenses) ያለአግባብ እንዲዘገዩ /መልስ እንዳያገኙ/ በማድረግና ጉዳዩ እንዲፋጠንልዎ አደርጋለሁ በማለት በተዘዋዋሪ በመጠየቅ፣

- አንዳንድ የፖሊስ፣ የመከላከያ ወይም የደህንነት አባላት በግለሰቦችና በድርጅቶች ላይ ተከታታይና ጭካኔ የተሞላበት ፍተሻና ክትትል በማድረግና በማስጨነቅ በተዘዋዋሪ የጉቦ ጥያቄ በማቅረብ፣

- በምርጫ ወቀት ሃብታሞችና አንዳንድ ኩባንያዎች የምርጫውን ዘመቻ በተዘዋዋሪ መንገድ ስፖንሰር እንዲያደርጉ የተለያዩ ማስፈራራቶችን፣ ጥያቄዎችንና ተጽእኖዎችን በማድረግ፣

- በመከላከያ ወይንም በፖሊስ አባላት የሚፈጸሙ ተገቢ ያልሆኑ የኬላ ቁጥጥር ተግባራትን በማካሄድ በተዘዋዋሪ ጉቦ የመጠየቅ፣

- ተገልጋዮች አገልግሎት ፍለጋ ወደ ተለያዩ ቢሮዎች ሲሄዱ ፋይላቸውን በመደበቅ፣ ነገ ከነገ ወዲያ ተመለስ በማለትና በማጉላላት በተዘዋዋሪ ጉቦ መጠየቅ…ወዘተ ናቸው።

2/ ምዝበራ (Embezzlement)

በመንግስትና በሕዝብ በተሰጠው ኃላፊነትና ሥልጣን በመጠቀም በሥራው አጋጣሚ የሚያገኘውን የመንግስትና የሕዝብ ሃብት፣ የመንግሥት ንብረቶችን ለማስተዳደር ባለውቀረቤታ በመጠቀም ወይም በቀጥታ በኃላፊነት እንዲጠብቃቸው የተሰጠውን ኃላፊነት ከለላ በማድረግ መስረቅ፣ መመዝበር መውሰድ ወይም ማስወሰድ ወይም ያለአግባብ መገልገልነው፡፡

በሌላ አገላለጽ አንድ የመንግስት ሠራተኛ አስተዳደር ተብሎ የተሰጠውን ወይም ለመንግስትሥራ ብቻ ተጠቀምበት ተብሎ በኃላፊነት የተረከበውን ንብረት ለግሉ ወይም ለዘመዱ ወይም ለሌላ ሰው መጠቀሚያ ሲያውለው ምዝበራ ተፈጸመ ይባላል፡፡

በአንዳንድ አገሮች መንግስት በአንድ ዓይነት መነሻ አዋጅ የውጭ ዜጎችን እና ቀድሞ በነበሩ የመንግስት ባለሥልጣናት ያለአግባብ ተይዘዋል የሚባሉ ንብረቶችን ከወረሰ በኋላ አግባብ በሌለው መንገድ በወቅቱ ስልጣን ላይ ላለው የፓርቲ አባላት፣ ወዳጆች፣ ደጋፊዎች፣ እንዲሸጡ፣ ተላልፈው እንዲሰጡ በማድረግ ምዝበራ ይፈጸማል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

- በዚምባብዌ መሬት ከነጭ ባለሃብቶች ተወርሶ በስልጣን ላይ ላለው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡
- በካሜሩን የቢራ ፋብሪካዎች፣ የስኳር ፋብሪካዎች፣ የነዳጅ ማጣሪያዎች እንዲሁም የትራንስፖርት ድርጅቶች ከሌሎች ተወስዶ ለገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

- በአይቮሪኮስት የቡናና የካካዋ እርሻዎች አግባብ ባልሆነ መንገድ ለግለሰቦች እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡

አንዳንድ ጸሐፊዎች ምዝበራን (Embezzlement) ስርቆት እንጂ ሙስና ሊባል አይገባውም ምክንያቱም ምዝበራ የሚፈጸመው በአንድ የመንግስት ሠራተኛ ሲሆን ሙስና ግን ሁለት እና ከሁለት በላይተዋንያን (actors) የመንግስት ሠራተኞች እና ሌሎች ግለሰቦች የሚሳተፉበት በመሆኑ ነው የሚል መከራከሪያ ሐሳብ ያቀርባሉ፡፡ ሆኖምይህ የመከራከሪያ ነጥብ የምዝበራ ድርጊት በመንግስት መ/ቤት ውስጥ በመንግስት ሃብትና ንብረት ላይ በመንግስት ሰራተኛ እና በሌሎችም ግብረ አበርነት የሚፈጸም በመሆኑ የሙስና ወንጀል ሆኖ እንዲፈረጅ ያደርገዋል፡፡

### 3.**ማጭበርበር** (Fraud)

ይህ ድርጊት በዋነኛነት የኢኮኖሚ ወንጀል በመባል የሚፈረጅ ሲሆን በከፍተኛ ተንኮልና ቅንብር የሚፈጸም ነው፡፡ ይኸውም የመንግስት ተቋማትና ወኪሎች ህገወጥ ተግባራን ህጋዊ ሽፋን በመስጠት ሕገወጥ በሆነ የንግድ ሥራ ላይ ሲሰማሩ/በኮትሮባንድ ንግድ ውስጥ ሲገቡ፣ የተጭበረበሩ ሰነዶች በማዘጋጀትና እንዲዘጋጁ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሲሳተፉ፣ እንዲጠብቁና እንዲቆጣጠሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግስት ባለሥልጣኖች በንግድም ሆነ በሰነዶች ዙሪያ ሙስና ሲፈጸም እያዩ እንዳላዩ በመሆን የሚፈጽሙት ድርጊት … ወዘተ/ነው፡፡

**በከፍተኛ ደረጃ ማጭበርበር ከሚፈረጁት ድርጊቶች ፡-**

- ኅስት የንግድ ተቋማትን በማቋቋም መነገድ፤ ለኀስት ሰራተኞች ፔሮል አዘጋጅቶ መክፈል፣
- ሰነዶችን በመሠረዝና በመደለዝ፣ የተሳሳተ የግዥ ማስረጃ በማቅረብ፣ የሐሰት ሰነዶችን በማዘጋጀት ወዘተ..በመሳሰሉት

- ማጭበርበሪያ ዘዴዎችንመጠቀም፣
- የመርዛማ ኬሚካሎችና ዝቃጮች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ወይም በጠረፎች አካባቢ እንዲጣሉ ፈቃድ መስጠት፣
- ሕገወጥ የባንክ ኖቶችን በከፍተኛ ደረጃ ማሳተምና ማሰራጨት፣
- የመንግስት ተቋማት፣ የግል ተቋማት ወይም ግለሰቦች ለሰጧቸው አገልግሎቶች ክፍያ ሳይከፍሉ ሲቀሩ/ሲከለክሉ/፣ የመንግስት ወይም የፓርቲ ባለሥልጣናት በአደገኛ እጾችና በሰዎች ሕገወጥ ዝውውር ሲሳተፉ፣
- ገንዘብን ከአገር ማሸሽና በሌላ አገር ሕጋዊ አስመስሎ ሥራ ላይ ማዋል (Money laundering)፣
- ጥራቱ ዝቅተኛ የሆነ የአንድ አገር ምርትን ከፍተኛ ጥራት ያለው ምርት የምታመርት አገር ምርት ለማስመሰል ሃሰተኛ የምስክር ወረቀት /ማረጋገጫ/ መስጠት ወይም መለያ ባጅ መለጠፍ፣ እንዲለጠፍ ፈቃድ መስጠትና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ለምሳሌ፡- ጥራት የጎደለውን ጫማ በከፍተኛ ጥራት የጫማ አምራች በሆነ ድርጅት ወይም ሀገር ስም ሃሰተኛ ባጅ መለጠፍ ወይም ላስመጪው የተጭበረበረ ምስክር ወረቀት ማዘጋጀትና መስጠት፣
- ሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ መታወቂያ ወረቀት ወይንም ማንኛውንም ሃሰተኛ ማረጋገጫ መስጠት፣
- ጊዜ ያለፈባቸውና የተበላሹ ምግቦች፣ መድኃኒቶች … ወዘተ. በገበያ ላይ እንዲሸጡ ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት፣

4 አድልዎ መፈጸም (Nepotism, Favoritism, Clientlism)

ይህ የሙስና መገለጫ በቀጥታ የገንዘብ ጥቅምን የሚያስገኝ ባይመስልም በተዘዋዋሪ መንገድ ከረጅም ጊዜ ግንኙነት አኳያ ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ማስገኘት ይችላል፡፡ ይህ የሙስና ወንጀል በዝምድና፣በዘር፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖትና በፆታ፣ በአምቻ ጋብቻ፣ ወይም በወዳጅነት ላይ ተመርኩዞ ከህዝብና ከመንግስት የተሰጠን ሥልጣን በመጠቀም የግል ወይም የቡድን ፍላጎት ለማሟላትና ጥቅም ለማስገኘት ሲባል የሚፈጸም አድልዎነው፡፡

በሌላ አገላለፅ ለዘመድ ወይም ለወዳጅ የሚደረግ የውለታ ሥራ ሲሆን ይህም ሹመትን በዝምድና መስጠትን፣ በያዙት ሥልጣን ተጠቅሞ ዘመዶችን፣ ወዳጆችን ለመጥቀም ሕግና ደንብ በጣሰ መንገድ ኮንትራቶች መስጠትን፣ ሥራ ማስቀጠርን … ወዘተ. የሚያካትት ነው፡፡

ሀ. በዝምድና መስራት (Nepotism):- ለሥጋ ዘመድ፣ ለቤተሰብ፣ ለሚስት ዘመዶች… ወዘተ. አግባብ ባልሆነ መንገድ ለመጥቀም የሚፈጸም ሲሆን ይህም፡-

- በሥራ ቅጥር፣ በዝውውር፣ በዕድገት ውድድር፣
- ለትምህርት ዕድል በሚደረግ ምልመላ፣
- የመንግስት ንብረት ወደ ግል በሚዛወርበት ጊዜ በሚደረግ ውድድር ቤተዘመድን ማስቀደም ወዘተ፣

ለ. ማዳላት (Favoritism):- ለአንድ ወዳጅ ከቤተሰብ ወይም ከሥጋ ዝምድና ውጭ ላለ ሰው በእከክልኝ ልከክልህ አካሄድ የሚፈጸም ውለታ ሲሆን ይህም ዜጎች በነፃ ውድድር ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ሌላ ጊዜ ውለታ ለሚጠበቅበት ጓደኛ፣ የብሔረሰብ አባል፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባል … ወዘተ አሳልፎ መስጠትን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የሙስና ወንጀል ከተስፋፋና በብዛት የሚሠራበት ከሆነ የሕብረተሰቡን አንገት የሚያስደፋ፤ ዜጎች በአገራቸው ሠርተው ለመኖር ያላቸውን መብትና ተስፋ እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ አደገኛ ችግርነው፡፡

ሐ. በወዳጅነት መስራት (Clientlism)፡- ይህ አይነቱ አድልዎ በአገልግሎት ሰጪና ተቀባይ መካከል በተደጋጋሚ በሚፈጠር ግንኙነት መነሻ የሚፈጸም የሙስና ተግባር ነው፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ከሚፈጠር ተደጋጋሚ ግንኙነት የተነሳ ለደንበኞች ቅድሚያ በመስጠት ሰበብ በሌሎች ተገልጋዮች ላይ አድልዎን በመፈጸም በደል ያደርሳል፡፡

5.ስጦታ (Gift)

የሚሰጥን አገልግሎት መነሻ በማድረግ ለአገልግሎት ሰጪው ዋጋ ያለው ስጦታ በመስጠት በኃላፊው ወይም በሠራተኛው ላይ ተጽእኖ በማሳደር ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ በአንዳንድ አገሮች አንድ ሰራተኛ ሊቀበለው የሚገባ የስጦታ መጠን በህግ የተወሰነ ሲሆን ከተወሰነው መጠን በላይ በሚሆንበት ጊዜ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበትም በህጋቸው ያስቀምጣሉ፡፡

## 1.4. የሙስና መንስዔዎች

ሙስና የመንግሥትና የህዝብ ሃብትን የግል ወይም የቡድን ፍላጎትን በህገወጥ መንገድ ለማሟላት መልካም ሥነምግባር በሌላቸው ሰዎች የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ ለሙስና መከሰት የሥነምግባርውድቀት ወይም ብልሹ ሥነምግባር ዋነኛው መንስዔ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ሌሎች አባባሽ ምክንያቶችም አሉ: እነዚህን ምክንያቶች በዚህ ትምህርት ውስጥ እንመለከታቸዋለን:

ከመልካም ሥነምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን የሙስና መንስዔዎች ለአብነት ተመልከቱ፡-

- የመስረቅና የስግብግብነት ባህሪ መኖር፣
- ሳይሰሩ በአቋራጭ የመክበር፣ የተደላደለና የተንደላቀቀ ሕይወት የመኖር ፍላጐት፣
- ለተለያዩ ሱሶች መጋለጥ ለምሳሌ ቁማር፣ መጠጥ ወዘተ፣

- ለሌሎች ያለማሰብና ለሃገር የመቆርቆር ስሜት አለመኖር፣
- ግለሰቦች ከሕግ በላይ የመሆን ስሜት ሲሰማቸውና ሕጋዊ እርምጃ አይወሰድበንም ብሎ መገመት፣

- ግለሰቦች ኃላፊነት የማይሰማቸው መሆን ወይም የግድ የለሽነት ባህሪያትን እያዳበሩ መሄድ ሙስናን ለመፈጸም ምክንያት ይሆናሉ:

በመሆኑም በዚህ ትምህርት ውስጥ ለሙስና መከሰት ምክንያት ከሆነው ብልሹ ሥነምግባር በተጨማሪ ሌሎች መንስዔዎችን በስፋት የምናይበት ይሆናል: ለአቀራረብ እንዲመች ሙስና እንዲባባስ የሚያደርጉ ምክንያቶችን በአራት ክፍሎች ከፍለን እናያቸዋለን።

እነሱም: -

1. ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች፣
2. ፖለቲካዊምክንያቶች፣
3. ባህላዊ ምክንያቶች እና
4. ተቋማዊ ምክንያቶች ናቸው።

ለሙስና መባባስ ዋና ዋና በሆኑት ምክንያቶች ላይ ከመነጋገራችን በፊት ቀጥሎ የተሰጠውን መልመጃ ስሩ

መልመጃ አምስት: - መመሪያ

በቡድን በመሆን ለሙስናመከሰትና መንሰራፋት የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ የፖለቲካ ሁኔታ፣ ተቋማዊ ሁኔታ እና ባህላዊ ሁኔታ እያንዳንዳቸው እንዴት ምክኒያት እንደሚሆኑ ማብራሪያና ምሳሌዎችን በማቅረብ አስረዱ።

### 1.4.1. ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች

በከፍተኛ ደረጃ ለሙስና መንሰራፋት አባባሽ ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች መካከል ኢኮኖሚያዊ ሆኔታ አንዱ ነው:: በዓለማችን ባሉ በተለይ ባላደጉት አገሮች ያለው ድህነት፣ ሥራ አጥነትና በአጠቃላይ ኋላቀርነት በሚታይባቸው ታዳጊ ሃገሮች ውስጥ ሙስና ጎልቶ ይታያል:: ይህ ማለት ግን ሙስና ባላደጉ አገሮች ብቻ የሚታይ ችግር ነው ማለት አይደለም። በአደጉና ባላደጉ ሃገሮች የሚታይ ችግር ነው:: ይሁንና ከኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ:-

- በአብዛኛው ግለሰቦች የእለት ተእለት ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ከገቢያቸው ባሻገር ሙስናን እንደ አንድ የገቢ ምንጭ ሲጠቀሙበት ይስተዋላል።

- ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ የመጣው የኑሮ ውድነት ግለሰቦች የሚያገኙት ገቢ አነስተኛ መሆንና ፍላጐታቸውን ማሟላት አለመቻላቸው፣

- በቂና አስተማማኝ የሆነ የጡረታ ዋስትና አለመኖርና የሥራ ላይዋስትና አለማግኘት ጋር ተዳምሮ ግለሰቦች በስራቸው ሂደት በሙስና እንዲዘፈቁ ይገፋፋቸዋል። በአንድ አገር ውስጥ ያሉ የልማትና አልግሎት ሰጪ የሆኑ የኢኮኖሚ አውታሮች በመንግስት ስር ብቻ መሆን ሞኖፖሊን ወይም የተማከለ አሰራርን ስለሚፈጥር፣ የቁጥጥር ሥርአቱን በማዳከም የመንግስት ባለስልጣኖች በቁጥጥራቸው ስር ያለውን የህዝብ ስልጣንና ሃብት በቀላሉ ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም እንዲያውሉ በር ይከፍታል። በተጨማሪም መንግስት ብቸኛ አቅራቢ ስለሚሆንና ተወዳዳሪ ስለማይኖረው ማንኛውም አገልግሎት ፈላጊ አገልግሎቱን ለማግኘት የማይገባ ክፍያ ለመክፈል የሚገደድበትን ሁኔታ ስለሚያመቻች ሙስና እንዲባባስ ያደርጋል።

### 1.4.2. *ፖለቲካዊ ምክንያቶች*

ዲሞክራሲያዊ የሆነ፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት፣ ስልጣን አንድ ቦታ ሳይከማች የተከፋፈለበት ሥርዓት ለህዝብ ታማኝነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት የተሞላበትን አሰራር ስለሚያዳብር አብዛኛውን ጊዜ በተወሳሰበ የሙስና ችግር የመዘፈቅ እድሉ ዝቅተኛ ነው፡፡ በተቃራኒው ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ፣ የሕግ የበላይነት የሌለበት፣ የሥልጣን ክፍፍልና ነጻ ፍርድ ቤት የሌለበት ሥርዓት ዜጐች በሕግአግባብ በአገራቸው ሰርተው እንዲጠቀሙ ስለማያበረታታ፣ ሚዛናዊ ያልሆነ አስተዳደር ስለሚከተል ለተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ጥቅምና ፍላጐቶች ስለሚቆም ሙስና እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡ ለሙስና መንስኤ ከሆኑት ፖለቲካዊ ምክንያቶች መካከል፡-

- ደካማ የሆነ ፓርላሜንታዊ የቁጥጥርና የግምገማ ሥርዓት የተንሰራፋበት ወይም ጭራሹን የጠፋ ከሆነ፣
- የሙስና ወንጀሎች ሲፈጸሙ አጥፊዎችን ተከታትሎ ለፍርድ እንዲቀርቡናተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያበቃ

  የፖለቲካ ተነሳሽነት (Political will) ከሌለ፣
- የፍትህ ሥርዓቱ ግልጽነት የጐደለው አሰራርና በሙስና የተዘፈቀ ከሆነ፣
- ከመጠን በላይ የተማከለ አስተዳደርካለ፣
- ተጠያቂነት የጐደለው አሰራር ያለውና ይህም ያለገደብ እንዲቀጥል የተደረገ ከሆነ ለሙስና መከሰት መንስኤ ይሆናሉ፡፡

### 1.4.3. ጎጂ ባህላዊ ልምዶች፣ አስተሳሰቦች

በአንድ አገር ውስጥ ያሉ የተለያዩ አስተሳሰቦች፣ ባህላዊ ልምዶችና አካሄዶች ለሙስና መስፋፋት የየበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ ለምሳሌ በአገራችን “ሲሾም

ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል፣ የሺን ገንዘብ ብላው የሺን ወንድም ፍራው" የሚሉት አባባሎችና የመሳሰሉት አስተሳሰቦች ግለሰቦች ወደ መንግስት ሥራና ኃላፊነት ሲመጡ በሕገወጥ መንገድ የህዝብን ሀብት እንዲመዘብሩ ይገፋፋቸዋል ::

ከዚህም ሌላ ባለጉዳዮች የተለያዩ ጉርሻዎችን ወይም ስጦታዎችን በመስጠት ጉዳያቸው በተፋጠነና በተቀላጠፈ መንገድ እንዲከናወንላቸው ወይም በህገወጥ መንገድ ጥቅም ለማግኘት ድርጊታቸውን የማሳካት ፍላጎትና አስተሳሰብ መኖር ለሙስናና ብልሹ አሰራር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል::ዓለም ባንክ በ2006 ባወጣው ጽሁፍ በአንድ ተቋም ውስጥ ቀጥለው የተጠቀሱት አስተሳሰቦች የሚንጸባረቁ ከሆነ ብልሹ አሰራር ስለመኖሩ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች (Red Flags) መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ እነሱም፡-

- ለአንዴ ብቻ (ለአሁን ብቻ) ሙስና ብፈጽም ችግር የለውም፣
- ሙስና ብፈጽም ማንም ሊያውቀው ወይም ሊደርስበት ስለማይችል አያስጨንቀኝም፣
- ስራው እስከተሰራ ድረስ በየትኛውም መንገድ ቢሰራ ግድ የለኝም፣
- የሰራሁት መጥፎ ተግባር በጥሩ ሁኔታ እውነት እንዲመስል ስላደረግኩት ማንም አይደርስበትም፣
- ሙስናን ሁሉም የሚያደርገው ነው፣
- የሰነዱን ደብዛ ባጠፋበት ሳይወድ በግድ ጉቦ ሊሰጠኝ ይገደዳል፣
- ማንም እንዳይደርስበት በአስተማማኝ ድርጊቱን/ጥፋቱን/ ልንደብቀው እንችላለን፣
- በመስሪያ ቤቱ በተፈጸመው ጥፋት ማንም ስለማይጎዳ አላጋልጥም፣
- ከምሰጠው አገለግሎት ለግሌ ምንም ስለማላገኝ ለሥራው ቅድሚያ አልሰጥም፣
- "አስፈላጊ ከሆነ ይታሻል" እና ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል::

ዝምድናን፣ ማህበራዊ ትስስርንና ውለታን መሠረት አድርጐ ስራን ማከናወን ለሙስና መባባስ ሌላው ምክንያት ነው:: ሕግንና ደንብን ተከትሎ ከመስራት ይልቅ በልማዳዊ አካሄድ ዝምድናን፣ማህበራዊ ትስስርንና ውለታን መሠረት አድርጐ ስራን ማከናወን በአንዳንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሰውን መርዳት ወይንም ውለታን መዋል አልያም ውለታን መመለስ፤ ለሰዎች ጥሩ ከማሰብ እንጅ ከሙስና ጋር ምንም ተያያዥነት እንደሌለው አድርጎ የመመልከት አስተሳሰብ ሙስናን ያባብሳል።

### 1.4.4. ተቋማዊም ክንያቶች

ሀ. ልዩ ልዩ ደንቦችና መመሪያዎች አለመኖር፤ ያሉትም ግልጽነት የጎደላቸው መሆን ሙስናን የሚያባብሱ ተቋማዊ ምክንያቶች ናቸው።

ለምሳሌ:- በአንድ ተቋም ውስጥ ሰራተኞች እና የሥራመሪዎች የሚመሩበት ግልጽ የሆኑ ደንቦች የሥራ መመሪያዎች እና የሥነምግባር ደንብ የሌለ ከሆነ ለሙስና መንስዔ ይሆናል። ምክንያቱም ግልጽ የሆኑ ደንቦች የሥራ መመሪያዎችና የሥነ ምግባር ደንብ አለመኖር ሥልጣንን ያለአግባብ ለመጠቀምና ደንቦችና መመሪያዎችን ለህገወጥ ተግባር በሚያመች መንገድ በመተርጐም እና በመጠቀም ሙስናን ለመፈጸም ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

በተለይም በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ግልጽና ለሙስና በር የማይከፍቱ አሠራሮች የተዘረጉ ካልሆነ፣ ግልጽ እና ወጥነት ያለው የልዩ ልዩ ገቢዎች አሰባሰብ ሥርዓት ከሌለ፣ የግዥ እና የንብረት አወጋገድ መመሪያዎችን በአግባቡ ካልተተገበረ፣ ተገቢ የሆነ የገንዘብ እና የንብረት ገቢ ወጪ ቁጥጥር ሥርዓትን ተግባራዊ ካልተደረገ እና የመሳሰሉት ለሙስና መከሰት መንስዔ ይሆናሉ።

ለ. በተቋሙ ለሠራተኞችም ሆነ ለሥራ መሪዎች ምቹ የሥራ ሁኔታ አለመኖር በተቋሙ ውስጥ:-

በሥራቸው ትጉህና ውጤታማ የሆኑ ሠራተኞች ማበረታቻ የሚያገኙበት ሥርዓት ከሌለ፣ የደረጃ ዕድገት፣ የትምህርት ዕድልና ሌሎችም ጥቅማ ጥቅሞች በውድድር ላይ ካልተመሠረቱ፤ የተመሰረተና ችሎታን፣ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድን መሠረት ካላደረጉ የሚሰጥበት ደንብና ሥርዓት ቢኖርም አፈጻጸም ላይ ሥርዓቱና ደንቡ በማን አለብኝነት የሚጣስ ከሆነ የሠራተኛው የሥራ ሞራሉና ተነሳሽነቱ ይወድቃል። ከዚህ የተነሳ ለሥራ ሥነምግባር ያለው ግምት እንዲወርድ፣ ቀኝነቱና ታማኝነቱ እንዲሸረሸር እና በዚህም ሠራተኛው በሚያገኘው

አጋጣሚ ያጣውን ጥቅማ ጥቅም ሕገወጥ በሆነ መንገድ /ጉቦበ መቀበል፣ የመንግስት ገንዘብ በመሥረቅና በማጭበርበር ወዘተ./ ለማግኘት ይገፋፋል።

## 1.5. ሙስና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

የተለያዩ የጥናትና ምርምር ግኝቶች እንደሚያመለክቱት ሙስና ፈር ብዙ የሆኑ ጉዳቶችን በማድረስ አብዛኛውን ህዝብ ለከፋ ድህነት ከመዳረግ አልፎ የሰውን ልጅ ህልውና የሚፈታተን አደጋ ነው። ሙስና ብዙሃኑን የህብረተሰብ ክፍል ለከፋ ድህነት የሚዳርግ ወንጀል ሲሆን፣ የአደገኛ የጦር መሳሪያዎችና አደንዛዥ እጾች ዝውውር እንዲስፋፋ፣ የተፈጥሮ ሚዛን እንዲቃወስ አልፎ ተርፎም ሰላም፣ ፀጥታና ፍትህ አደጋ ላይ እንዲወድቁ የሚያደርግ ማህበራዊ ጠንቅነው።

የሙስና ጦስ አንዳንድ ሃገራትን ለመበተን አደጋ እንደዳረጋቸውም ታይቷል። በመሆኑም ለተለያዩ ወንጀሎች መበራከት ሙስና ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስድ መሆኑን እና የሚያስከትላቸውን ዋና ዋና ጉዳቶችን በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ለማየት እንሞክራለን::

ወደ ስልጠና ከመግባታችን በፊት ቀጥሎ የተመለከተውን መልመጃ በሚሰጣችሁ መመሪያ መሰረት ስሩ: -

መልመጃ ስድስት: - መመሪያ

ሀ. አሠልጣኙ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በቡድን በመሆን

1. ሙስና በአንድ አገር ላይ ምን አይነት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ጉዳት እንደሚያደርስ ምሳሌዎችን በማቅረብ አብራሩ፣ ሙስና በአገር ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ከባቢያዊ ጉዳቶችንና ቀውሶችን እንደሚያስከትል በርካታ የጥናትና ምርምር ግኝቶች አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዱን በዝርዝር እናያለን፡፡

### 1.5.1. ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች

ሙስና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በመፍጠር የአገር ልማት እንዲቀጭጭ፣ የኢኮኖሚ እድገት እንዲገታ፣ ኪሣራና ውድቀት እንዲፋጠን እና ድህነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ በማድረግ ዜጎች ወደ ከፋ የኑሮ አዘቅት ውስጥ እንዲወድቁ ያደርጋል፡፡ እንዴት?

- ለኢኮኖሚ እድገት የተነደፉ የልማት ፕሮጀክቶች ለህብረተሰቡ የጎላ ጥቅም በማይሰጡ ፕሮጀክቶች እንዲተኩ በማድረግ፣
- የመንግስት በጀት ለተገቢው እና ቅድሚያ ሊሰጠው ለሚገባው ተግባር እንዳይውል በጥቂቶች ለሚፈልጉት ተግባር እንዲውል በማድረግ፣
- የግብር አሰባሰብ ሥርዓትንና ደንብን በማዛባት ከገቢ ግብር እና ልዩ ልዩ የታክስ ገቢዎች ለመንግስት መግባት የሚገባውን የገቢ መጠን በመቀነስ በቂና አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎት  መስጫ ተቋማት እንዳይፈጠሩ እንቅፋትበመሆን፣
- ከፍተኛ የውጪ ኢንቨስተሮችን /ባለሃብቶችን/ ገንዘብና እውቀታቸውን በአገር ኢኮኖሚ እድገትና ልማት ላይ ለማዋል የሚያስችል

አገልግሎቶችን ለማግኘት ጉቦ እንዲከፍሉ በመጠየቅ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ገንዘብና እውቀታቸውን በአገር ኢኮኖሚ እድገትና ልማት ላይ ለማዋል የሚያደርጉትን ተሳትፎና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን በመገደብ፣

- ኢፍትሃዊ በሆነ አስተዳደር የስራተኛውን እድገት ቅጥርና ጥቅማ ጥቅም ችሎታን መሰረት ባደረገ መንገድ ባለማከናወንና ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዳይኖር በማድረግ የሰራተኛውን የሥራ ፍላጎትና ሞራል እጅጉን እንዲጎዳና የሥራ ውጤታማነቱንና ምርታማነት እንዲቀንስ በማድረግ፣

- የአገርን ሃብት ጥቂት ባለስልጣናትና ባለሃብቶች እንዲቀራመቱት ሁኔታዎችን በማመቻቸት አብዛኛውን ህዝብ ለድህነት፣ ለችግርና ለከፋ የጉስቁልና ኑሮበመዳረግ፣

- ለህዝብ የሚቀርቡ የፍጆታ ዕቃዎች መጠንና ጥራትን በመቀነስ የግብይትን ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በማናር ህዝብን ለከፋ የኢኮኖሚ ችግር ይዳርጋል፡፡

### 1.5.2. ማህበራዊ ጉዳቶች

ሙስና በህዝቦች ዘንድ የሞራል ውድቀት፣ የሥነምግባር ቀውስ እና የሕግ የበላይነት እንዳይሰፍን በማድረግ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ /ሥራ አጥነት፣ ጎዳና ተዳዳሪነት፣ ዋልጌነት፣ ጥፋተኛነትና ሥርዓተ አልበኝነት፣ ሴተኛ አዳሪነተ ወዘተ/ ያስከትላል፡፡ እንዴት?

- ሙስና በሰፈነበት አገር በዋነኛነት ሰፊው ህብረተሰብ የችግሩ ተጠቂ በመሆኑ በሚያጋጥመው የኢኮኖሚ ቀውስ ሳቢያ አብዛኛው ህዝብ ለድህነት ይዳረጋል፡፡ ሰርቼ የተሻለ ኑሮ አኖራለሁ ብሎ የሚመኘው

ህዝብ ለሥራ አጥነት፣ ለጎዳና ተዳዳሪነት እና ለሴተኛ አዳሪነት ይጋለጣል፣ እጅግ ሲከፋም ለስደት እንዲዳረግ ምክንያትይሆናል፡፡

- ሙስና በህግ እኩል የመዳኘትንና የመንግስት አገልግሎት ጥራትን ስለሚቀነስ የሕግ የበላይነት ስሜትን ከህብረተሰቡ ዘንድ በማጥፋት ማህበረሰቡን ላልተረጋጋ ህይወት በመዳረግ ዋልጌነት፣ ጥፋተኛነትና ሥርዓተ አልበኝነት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በዚህም የህዝቡ ስላማዊ ህይወት አደጋ ላይይወድቃል፡፡

- በሙስና ሰበብ ለማህበራዊ አገልግሎት ለትምህርትና ለልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታ መዋል የሚገባው የመንግስት ሃብት ለጥቂቶች እንዲውል ስለሚደያደርግ፣ አብዛኛው ህብረተሰብ የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ መሆን አይችልም፡፡ የትምህርት እድል የንጹህ ውሃ አቅርቦትና በቂ የህክምና አገልግሎት በማጣት ለመሃይምነት፣ ለኋላ ቀርነት እና ለከፍተኛ የጤና ችግርይጋለጣል፡፡

### 1.5.3. ፖለቲካዊ ጉዳቶች

ሙስና ህዝብ በመንግስትና በሕግ የበላይነት ላይ አመኔታ እንዲያጣና በዲሞክራሲ ሥርዓት ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረው በማድረግ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡

እንዴት?

- የመንግስት ሥራዎች ከተገቢው አሰራርና ከሕግ ውጪ እንዲከናወኑ በማድረግ፣

- ሙስና ዜጐች በሀገራቸው ብሔራዊ ሃብት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መብታቸው እንዲነካና አድሎ እንዲፈጸምባቸው ስለሚጋብዝ ህዝቦች በመንግስት ላይ የሚኖራቸው እምነት እንዲሸረሸርና በሚኖሩበት ሀገር

ውስጥ የቤተኝነት ስሜት እንዳይሰማቸው በማድረግና በዚህም የተነሳ በመንግስትና በህዝብ ዘንድ ትልቅ ክፍተት እንዲፈጠርያደርጋል፣

- በአንድ አገር ውስጥ የፖለቲካ መረጋጋት እንዲጠፋ በማድረግ ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ እንዳይኖር በማድረግ ለህገ ወጥ ሹም ሽር እንዲጋለጥ ምክንያት ይሆናል፣

- የመልካም አስተዳደር ችግር መንግስት በህዝብ ዘንድአመኔታ በማሳጣት አገርን ወደ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት እንዲያመራ ከማድረግ ባሻገር የሕግ የበላይነትን በማደብዘዝ ስርዓተ አልበኝነትና የዲሞክራሲያዊ መብት ረገጣ እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

- የህግ የበላይነት መደብዘዝና ሥርዓተ አልበኝነት መንገስ ደግሞ ሕዝብየተረጋጋ ኑሮ እንዳይመራ ከማድረግ ባሻገር አንድ መንግስት በመንግስትነቱ እንዳይቀጥል ምክንያት ይሆናል።

የሙስና በአንድ አገር ውስጥ መንሰራፋት የአገር ደህንነት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል። በተለይም ሙስና በሚያስከትለው ያልተመጣጠነ የሃብት ክፍፍል በአንድ አገር ውስጥ ግጭቶችና አልፎ ተርፎም የእርስ በርስ ጦርነቶች የሚከሰቱበት አጋጣሚ እንዲፈጠር ያደርጋል።

በሌላ በኩል ሙስና በአንድ አገር ውስጥ የመንግስት አለመረጋጋት ስለሚፈጥር የአገርን ህልውና ጥያቄ ውስጥ ይከታል። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ሙስና በአውሮፓዋ ሀገር ጣሊያን ተደጋጋሚ የካቢኔ መበተን እንዲደርስ ማድረጉን በዋቢነት ማንሳት ይቻላል:: በአፍሪካም በሴራሊዩን፣ በላይቤሪያ፣ በኮንጐ፣ በሶማሊያ የደረሰው መጠነሰፊ ቀውስ ከሙስና ጋር የተያያዘ መሆኑ ይታወቃል።

ሙስና ለአገሮች ሁለንተናዊ እድገት ማነቆ ከመሆኑም በላይ ህልውናቸውንም በመፈታተን ሰላምና የፖለቲካ መረጋጋት እንዳይኖር ያደርጋል። ይህም ማለት

ሙስና ለሃገሮች የፖለቲካ አለመረጋጋትና ለርስ በርስ ጦርነቶችና ግጭቶች መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ በአብዛኛው ጊዜ የሚስተዋለው የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍልን መሰረት በማድረግ አላስፈላጊ የሆነ የጥቅም ትስስር በሚኖርበት ወቅት በድርጊቱ የተወሰኑ ቡድኖች ብቻ የሚጠቀሙበት ሲሆን ነው፡፡ ከሥርዓቱ ወይንም ከአገዛዙ ምንም አይነትአልያም ጥቂት ጥቅም የሚያገኘው ቡድን ራሱን በማንቀሳቀስ እኩል ወይም የተሻለ ድርሻ ለማግኘት የሃይል አማራጭን በመከተል ትግል ይጀምራል፡፡ በዚህ ወቅት አስፈላጊ ያልሆኑና አውዳሚ የርስበርስ ግጭቶችይነሳሉ፡፡

ከዚህም ሌላ ሃገሮች የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ በሚዘፈቁበት ወቅት የሙስናውም መጠን የበለጠ ስለሚወሳሰብና ስለሚስፋፋ ጦርነቱ ለረጅም አመታት እንዳይበርድ ምክንያት ይሆናል፡፡ ሙሰና የእርስ በርስ ጦርነትን እንደሚያመጣ ሁሉ የእርስ በርስ ጦርነትም የሙስና ወንጀል የበለጠ እንዲስፋፋና እንዲወሳሰብ በር ይከፍታል፡፡ ይኸውም አንድ አገር በእርስ በርስ ጦርነት ስትታመስ ሌሎች አገሮች በሁኔታው ተጠቃሚ ሲሆኑ ጥቅማቸውንም የሚያቀራኙት ከተለያዩ ግለሰቦች/መሪዎች/ ጋር በሙስና በመተሳሰር ነው፡፡ እነዚህ አገራት ጦርነቱ እንዳይበርድ በማድረግ በእዛ ሃገር ውሰጥ የሚገኘውን የማእድን፣የነዳጅና ሌሎችን ሃብቶች በመዝረፍ የጦር መሳሪያ ንግዳቸውን በመጧጧፍ እራሳቸውንሲጠቅሙ ይስተዋላሉ፡፡

ለዚህም በላይቤሪያ፣ በሴራሊዮን፣ በአንጎላና አፍጋኒስታን የተከሰቱ ግጭቶችን ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ

- የሙስና መንሰራፋት የተለያዩ እቅዶች እንዳይተገበሩና ያልተስተካከለ እድገት እንዲኖር በማድረግ በመንግስት ላይ የተለያዩ ተቃውሞዎችና ጥያቄዎች እንዲነሱ በማድረግ በከፋ መልኩም ለጉሳ ግጭቶች፣ ለብሔርና ለኃይማኖት ጦርነቶች በር በመክፈት፣

- ሙስና የዲሞክራሲ ሥርዓት መሠረት የሆኑትን የግልጽነትና የተጠያቂነት መርሆዎችን የሚያፋልስ የሰዎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚገድብ ተግባር በመሆኑ ሕዝብ በዲሞክራሲ ሥርዓት ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረውና ለሥርዓቱ ግንባታ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዳያደርግ እንቅፋት በመሆን በዚህም ህዝብ መንግስት በሚያቅዳቸው ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ እንዳያበረክት ምክንያት ይሆናል፡፡

### 1.5.4. ከባቢያዊ ጉዳቶች

ሙስና የስግብግብነት ስሜትን አግንኖ ስለሚያወጣ የተፈጥሮ ሚዛንን በማዛባት ከባቢያዊ ሁኔታዎችን የሚያዛቡ ተግባሮችን በመፈጸም የሰውን ልጅ የመኖር ህልውና የሚፈታተኑ ጉዳቶችን ያስከትላል፡፡ እንዴት?

- የተፈጥሮ ሃብቶች ከማንኛውምሃብት ባልተናነስ መልኩ ለሙስና የተጋለጡ ናቸው፡፡ ይህም በሁለት መንገድ ሲሆን አንደኛው የተፈጥሮ ሃብቶችን ኃላፊነት በጐደለው መንገድ መመዝበር ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ለአካባቢ ብክለት ከፍተኛ ሚና የሚኖራቸውን፣ የአካባቢ ዑደትን ሊያዛቡ የሚችሉ አደገኛ የኬሚካል ተረፈ ምርቶችን በየብስ፣ በአየርና በምድር ላይ ማስወገድን የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

- በሙስና ግንኙነት ለደን የተከለሉ የደን ልማት ቦታዎች እንዲጨፈጨፉ፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ሃብቶች እንዲሰረቁ፣ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡና ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የተከለከሉ ኬሚካሎች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ በመፍቀድ የአገር የተፈጥሮ ሃብት ያለአግባብ እንዲባክን በማድረግ፣ በዚህም ለአከባቢ

አየር መዛባት፣ መበከል እና ለከፋ የኢኮኖሚ ወድቀት እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

- ከህገ ወጥ የመሬት ወረራ ጋር ተያይዞ ከተሞች ማስተር ፕላናቸውን ጠብቀው ለልማትና ለእድገት አመቺ የሆነ አሰፋፈር እንዳይኖራቸው በማድረግ በከተሞች እድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

በአካባቢ የተፈጥሮ ሃብቶች ላይ ከሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችለው የሕግ ወጥ የደን ቆረጣ ሲሆን፣ ለምሳሌ በካምቦዲያ በ1997 ዓ.ም. ለመንግስት ባለስልጣናት የተሰጠ ጉቦ ወደ 200 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ሲሆን፣ ይህ የካምቦዲያ መንግስት በህጋዊ መንገድ ከተፈጥሮ ደን ሽያጭ ካገኘው በ13 እጥፍ ይበልጣል፡፡ በኢንዶኔዥያም በሃገሪቱ ጥቅም ላይ የእንጨት ውጤቶች ከ50-70 በመቶ በሕገ-ወጥ መንገድ የሚመረት ሲሆን ይህም የሃገሪቱን የደን ሃብት በዓመት ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር በላይ እንዲወድም ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ በሩሲያ 20 በመቶ የእንጨት ምርት በሕገወጥና ኃላፊነት በጐደለው መንገድይቆረጣል፡፡

## ክፍል ሁለት፡ የሙስና መከላከያ ስልቶች

### መግቢያ

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው፡፡ ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህርይ ያለውን ሙስና ለመዋጋት በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የተቀናጀ ስልት መንደፍ ተገቢ ነው፡፡ ምንም እንኳን ሙስናን ለመዋጋት አንድና ብቸኛ አማራጭ መንገድ ባይገኝም ወይም አንዳንድ ጸሃፊዎች እንደ ሚሉት ቢሆንም፣ በዘርፉ ምርምር ያካሄዱ አብዛኞቹ ባለሞያዎች ሙስናን ለመዋጋት የሚነደፉ ስልቶች አስቀድሞ በመካላከል፣ ህግን በማስፈጸም፣ በየተቋማት ብሄራዊ የትስስር ሥርዓት (National

Integrity System) እና የህብረተሰቡን ንቃተ ህሊና ከፍ በማድረግ ላይ ያተኮሩ ሊሆኑ ይገባል ይላሉ፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ በዚህ ሞጁል ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ያግዛሉ የተባሉ የሙስና መከላከል ስትራቴጂዎች ቀርበዋል፡፡ እነሱም አስተዳደራዊ አሰራርና ቁጥጥርን መሰረት ያደረገ የሙስና መከላከያ ስልቶች፣ በተቋማት ብሄራዊ የትስስር ስርአት፣ ህግን በማስፈጸም፣ የህብረተሰብ ግንዘቤን በማሳደግና በአሠራር ሥርዓት ሙስናን አስቀድሞ የመከላከል ስልቶች ናቸው፡፡

ዓላማ፡ ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ላይ ያላቸውን ቀደምት እውቀት ለማነሳሳት ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመሆን ተወያዩና ሃሳባችሁን ግለጹ፡፡

## 2.1 የሙስና መከላከል ምንነት

**ተግባር አንድ**

ሀ. መከላከል ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ሙስናን መከላከል ማለትስ ምን ማለት ነው?

ሐ. ቀጥሎ የቀረቡት ሁለት አባባሎች ስለመከላከል የሚያስተላልፉትን መልእክት ከገለጻችሁ በኂላ ለሙስና መከላከል ያላቸውን አንድምታ አስረዱ፡፡

፩. “The art of life is the art of avoiding pain” Thomas Jefferson/1743-1824/

፪. “ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ”

### 2.1.1 መከላከል

መከላከል “Prevention” የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚገልጽ ቃል ነው፡፡ የካምብሪጅ አድቫንስድ ዲክሽነሪ “Prevention” የሚለውን ቃል “when you stop

something from happening" በሚል ይፈታዋል፡፡ መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

### 2.1.2 ሙስናን መከላከል፡

ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡ አንዳንድ ጸሃፊዎች የሙስና መከላከል ቴክኒክ ጠቅለል ተደርጎ በሁለት ሊከፈል ይችላል ይላሉ፡፡ እነሱም ቀጥተኛ ቴክኒክ (Direct techniques) እና ተዘዋዋሪ/ቀጥተኛ ያልሆነ (In-direct techniques) የሚባሉት ናቸው፡፡

ቀጥተኛ የሙስና መታገያ ቴክኒክ - የሥራ ማስፈጸሚያ ህጎች፣ የአሰራር ማስፈጸሚያ ደንቦችና መመሪያዎች ለምሳሌ የፋይናንስ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር ቁጥጥር ስርዓት መመሪያና የፀረ-ሙስና ሕጎችና ደንቦችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ እነዚህ ህጎችና ደንቦች ሥራዎቹ እንዴት መከናወን እንዳለባቸው አስገዳጅ ድንጋጌዎችን የሚይዙ ሲሆን፣ የህጎቹና ደንቦቹ አፈጻጸም ውጤት በድንጋጌዎች መሰረት መሆኑንና አለመሆኑን የሚቆጣጠሩና የሚከታተሉ፤ ሕግና ደንቦቹ ተጥሰው ከሆነም እርማት እንዲወስድ ሃሳብ የሚያቀርቡ ወይም በተቀመጡት ሕጎች መሰረት ራሳቸውን ችለው እርምጃ የሚወስዱ ተቋማትን ያቋቁማል፡፡

ቀጥተኛ ያልሆነው የመታገያ ቴክኒክ- በመንግስት የፖለቲካና የአስተዳደር እንዲሁም በዜጎች ብሄራዊ ቁርጠኝነት፣ በሥነምግባር ደንቦች፣ በሃብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ዘዴ እና በመገናኛ ብዙሃን ሚና ላይ የሚወደቅ ነው፡፡

### 2.1.3 የሙስና መከላከል ተግባር አንጻራዊ ጠቀሜታዎች

የሙስና መከላከል ስራ በዋነኛነት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡-

- በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን ሃገራዊ ሃብት ለታለመለትሥራ ለማዋል ያስችላል፤
- ችግሩ ከተከሰተ በኂላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤
- በቀላሉ ተምረውና ተስተካክለው ለሃገር ጠቃሚ በሆነ ተግባር ላይ ሊሰማሩ የሚችሉ ዜጎችን በችግሩ ውስጥ ተዘፍቀው እንዲባክኑ ከማድረግ ያድናል፤
- በችግሩ ምክንያት በወንጀለኞች ቤተሰቦች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማህበራዊ ቀውስ ይቀርፋል፤
- ወንጀለኞችን ለማስተዳደር የሚወጣ ወጪን (ከማረሚያ ቤትና ከሌሎች ተያያዥ ከሆኑ ወጪዎች) ይቆጥባል፤
- በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራርክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

> "An Ounce of prevention is worth a pound of cure" UK

## 2.2 አስተዳደራዊ አሰራርና ውስጣዊ ቁጥጥርን በማጠናከር ሙስናን መከላከል አጭር መግለጫ

አስተዳደራዊው አሠራር የተቋቋሙትን ዓላማዎች ለማሳካት የአንድ ተቋም እንቅስቃሴ አደረጃጀት እና ቅንጅት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከቁሳቁሶች፣ ከማሽኖች እና ከገንዘብ ጋር እንደ ምርት ምክንያት ተዋህዷል፡፡ አስተዳደራዊ ሂደት የአንድ ጊዜ ልምምድ መሆን የለበትም፡፡ የሂደቶችን ቀጣይነት ያለው ግምገማ ማካተት እና አጠቃላይ ፍሰታቸውን ለማሻሻል እርምጃዎችን ማካተት አለበት፡፡ ይህ ሁሉ የድርጅቱን ቀጣይነት ያለው የምዘና እና መሻሻል ዑደት ያካትታል፡፡ የአስተዳደር ሂደት የሚከናወነው በአንድ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ ኩባንያው መካከለኛ ወይም ትልቅ ከሆነ ብዙውን ጊዜ የሚከናወነው በመምሪያው ዳይሬክተሮች ነው ፡፡

አስተዳደራዊ አሠራር ማለት ተቋማት መከተል የሚገባቸው የሥራ ሂደት ፍሰት ናቸው፡፡ እነሱም አራት ተግግባራትን የሚይዙ ሲሆን **ማቀድ፣ ማደራጀት/ማዋቀር፣ ማከናወን/መፈፀም** እና **መቆጣጠር** የሚሉት ናቸው፡

ሙስናን ለመከላከል እንደ አንድ ጠንካራ ስልት ተደርገው ከሚወሰዱ የመከላከያ ስልቶች መካከል አስተዳደራዊ አሰራርና ውስጣዊ ቀጥጥርን በማጠናከር ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በዚህ ስልት ተቋሙ አሰራሩን እየፈተሸ ለሙስና የሚያጋልጡ አሰራሮችን የሚያሻሽልበት እንዲሁም በተቋሙ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍንበት አሠራር ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የሙስና መከላከል፣ የተጠያቂነትና የግልጽነት ምንነት እንዲሁም በተቋም ውስጥ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ሙስናን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችና የመወያያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

ዓላማ፡- ከዚህ ስልጠና በኂላ ሰልጣኞች፡-

አስተዳደራዊ ወይም ቁጥጥርን መሰረት ያደረገ (Regulatory) ስልት ሙስናን ለመከላከል እንዴት እንደሚያግዝ አውቀው ይገልጻሉ፡፡

**የተመደበ ጊዜ፡- 2 ሰዓት**

### 2.2.1 ግልጽነትና ተጠያቂነት

የግልጽነትና ተጠያቂነት ጉዳይ መነሳት የጀመረው የመንግስት ተቋማት መከሰት ከጀመሩበት ጊዜ እንደሆነ አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ አሪስቶትል “The politics” በሚለው መጽሃፉ ውስጥ የመንግስት ገንዘብ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲሰበሰብ፣ ለተሰበሰበውም ገንዘብ ተጠያቂ እንዲኖር ለማድረግ የገንዘቡ መጠን በተለያዩ አካላት ሊታወቅ ይገባል በማለት የሰነዘረውን ሃሳብ መመልከት እንችላለን፤

> “To protect the treasury from being defrauded, let all public money be issued openly infront of the whole city, and let copies of the account be deposited in the various wards.” Aristotle

ለሙስና መከሰት በርካታ ሁኔታዎች ቢኖሩም በመንግስት አሰራር ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት አለመኖር ዋነኞቹ ናቸው፡፡

ግልጽነትና ተጠያቂነት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ከመመልከታችን በፊት በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትእዛዛቸው መሰረት እንስራ፡፡

**ተግባር ሁለት**

ዓላማ፡ በግልጽነትና ተጠያቂነት ዙሪያ ሰልጣኞች ልምድ እንዲለዋወጡ ማድረግ ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ ሃሳባችሁን ግለጹ

ሀ. "ግልጽነትና ተጠያቂነት" ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በመንግስት ተቋማት የግልጽነትና ተጠያቂነ ትአሰራ ርባይኖር ምን ሊከሰት ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ሐ. ግልጽነትና ተጠያቂነት ሙስናን ለመከላከል ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው? ምሳሌዎችን በመጥቀስ ሃሳባችሁን ለማጠናከር ሞክሩ

1. ግልጽነት

የኦክስፎርድ አድቫንስድ መዝገበ ቃላት ግልጽነት (Transparency) የሚለውን ቃል በሚከተለው መንገድ ይፈታዋል፡-

1. "The quality of something…that allows somebody to see the truth easily."
2. "The quality of something, such as a situation or an argument, that makes it easy to understand"

ከዚህ ብያኔ እንደምንረዳው ግልጽነት የአንድን ነገር እውነትነት የማሳየት ጥራት ወይም አቅም፣ እንዲሁም አንድን ሁኔታ ሊረዱት በሚቻል መንገድ ቀላል አድርጎ የማቅረብ ሁኔታ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡ በመንግስት አሰራር ውስጥ ግልጽነት ማለት ምን ማለት ነው?

- ሕዝቡ በመንግስት ውሣኔዎች ላይ በብቃት መሳተፍ እንዲችል ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ማግኘት ሲችል ነው፡፡ ህዝቡ የመረጠው መንግስት በትክክል መስራቱን ለመቆጣጠር የሚችለው ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ሲያገኝ ነው፡፡ በግልጽነት የአሰራር ስርአት ህብረተሰቡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻለ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆንም፡፡

የግልጽነት አሰራር ህብረተሰቡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኝ ከማድረጉም ባሻገር ጉድለቶች እንዲስተካከሉ፣ ርምጃም እንዲወስድ ለማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም የግልጽነት አንዱ መገለጫ የህዝቡን መረጃ የማግኘት መብት ማረጋገጥነው፡፡

- እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ህግ አስፈፃሚው አካል የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች የሚያቀርባቸው የሕግ ረቂቆች ወዘተ... ጉዳዮች ላይ ህብረተሰቡ አስቀድሞ የተወያየባቸውና አስተያየት የሰጠባቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡
- በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ህብረተሰቡ የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡ ለምሳሌ በአንድ የግንባታ ፈቃድ ሰጪ ተቋም ውስጥ “የግባታ ፈቃድ ለማውጣት ሁለት ቀን ይወስዳል” የሚል አሰራር ቢኖርና ለተገልጋዩ ይኸው አሰራር ግልጽ ያልተደረገለት ከሆነ ፈጻሚው አካል የፈለገውን ያህል ቀን ቢያመላልሰው መብቱን መጠየቅና ማስከበር አይችልም፤ ያጉላላውን ሰራተኛም ተጠያቂ

ማድረግ አይችልም፡፤ ይልቁንም በሚፈጠረው መንገላታት ለሙሰኛ የመንግስት ሰራተኛ የተጋለጠ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በመንግስት አሰራር ውስጥ ግልጽነጽትን ማስፈን ሙስናን ለመከላከል አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡

**2. ተጠያቂነት**

ተጠያቂነት የሚለው ቃል የንግሊዝኛውን Accountability የሚወክል ነው፡፡ የኦክስፎርድ አድቫንስድ መዝገበ ቃላት “Accountable - Responsible, answerable” በማለት ይፈታዋል፡፡

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት/በቅጣት ወይም ካሳ የማስከፈል ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስልጣንና አቅም ያለው አካል ሊኖር ይገባል፡፡

የተጠያቂነት ጽንሰ ሃሳብ ኃላፊነትን በመወጣትም ይገለጻል፡፡ ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

የተተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ እንዲሁም የህትመት ማቴርያሎችን በማውጣትና ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡

በአንድ ተቋም ውስጥ የተጠያቂነት አሰራር ከሌለ፣ በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሃላፊዎችና ሰራተኞች የተሰጣቸውን ሃላፊነት እንደወደዱ የሚጠቀሙበትና ሙስናን ለመፈጸም የተመቻቸ ቦታ ይሆንላቸዋል፡፡ በርካታ ጥናቶች የተጠያቂነት ስርዓት አለመኖር ከሙስና ጋርቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለቸው ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም በመንግስት አሰራር ውስጥ ተጠያቂነትን ማስፈን ሙስናን ለመከላከል ዓይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡

Robert Kilitgaard የተባለ የዘርፉ ተመራማሪ ተጠያቂነትና ሙስና ያላቸውን ትስስር እንደሚከተለው በቀመር ይገልጸዋል፡፡

C= M+D-A (Corruption equals monopoly plus Discretion minus Accountability) Robert Kilitgaard's (1988) formula.

ሙስና = የስልጣን ሞኖፖሊ ሲደመር የመወሰን ስልጣን ሲቀነስ ተጠያቂነት

የግልጽነትና የተጠያቂነት አለመኖር ከሚያስከትሉ ትጉዳቶች መከላከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

- ሰራተኛው ማድረግ ያለበትንና የሌለበትን ስለማያውቅ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት አይችልም፡፡
- የሚቆጣጠረው አካልም ይህንን ሳትፈጽም ቀርተሀል ብሎ ተጠያቂ ሊያደርገው አይችልም፡፡
- አገልግሎት ፈላጊም በቀላሉ የሚፈልገውን አገልግሎት እንዳያገኝ ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር መብቱን ለማስከበር፣ ለመጠየቅ ስለሚቸገር ለሙስና ተጋላጭ እንዲሆን በር ይከፍታል፡፡
- ለስርዓተ አልበኝነት ምክንያት ይሆናል፡፡

- ► በአጠቃላይ ግልጽነት የሌለበት አሰራር ስርአት ሙስና ለመፈፀም

ምቹ ይሆናል ማለት ነው፡ የመወያያ ጥያቄ

የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራርን በተመለከተ የኢፌዲሪ ህገመንግስት ምን ይላል? (አንቀጽ ፲፪ የመንግስት አሰራርና ተጠያቂነት)

**ተግባር ሶስት**

ዓላማ፡ ሰልጣኞች የየመስሪያቤታቸውን ልምምድ እንዲለዋወጡ ማድረግ

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩባቸውና ሃሳባችሁን ግለጹ፡፡

ሀ. በአንድ መስሪያ ቤት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ዘርዝሩ፡፡

ለ. በአንድ መስሪያ ቤት ተገልጋይ የሆነ ደንበኛ ተገቢውን መረጃ ባያገኝ እንዴት ለሙስና እንደሚጋለጥ ተቋማትን እንደ ምሳሌ እያነሳችሁ ተወያዩበት፡፡

ሐ. በምትሰሩበት ቦታ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር የሚሰሩ ስራዎች ላይ ተነጋገሩ፡፡

## 2.2.2 የሥነ-ምግባር ደንብ

በሙስና መከላከል ስልት ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውሰጥ ተቀባይነት ያለው የሥነምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የስነ-ምግባር ደንብ በተቋማት ውስጥ የባህሪ መመሪያ ነው፣ ይህም በውጤቶች ላይ በመመርኮዝ የውስጥ እርምጃዎችን ሥነ-ምግባር ይቆጣጠራል፡፡ ይህ የቁጥጥር ማዕቀፍ በተቋሙ ፖሊሲዎች እና ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ እንደ ሥነ-ምግባርና የተግባር ሞዴል መርሆዎች እና እሴቶች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም

ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡

የሥነምግባር ደንቦች ዝግጅት ዓላማ በመስሪያ ቤት ውስጥ ዘላቂ የሆነ የሥነምግባር ባህርይ ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም የሥነምግባር ደንቦች ተዘጋጅተው የሼልፍ ማዳመቂያ መሆን የለባቸውም፤ ወይም ለሰራተኞች መበተን ብቻ የመጨረሻ ግብ ሊሆን አይችልም፡፡ ይልቁንም ሰራተኞች ደንቡን የራሳቸው እንዲያደርጉት ወይም በደንቡ ውስጥ እንደተገለጸው ዓይነት ባህርይ እንዲላበሱ በየጊዜው ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም ደንቡን ከተቋሙ አሰራር ጋር በማስተሳሰር በቅጥር፣ በእድገት… ወዘተ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ የደንቡ ተግባራዊነት በሥነምግባራቸው አርአያ የሚሆኑ ሰራተኞች እውቅና የሚያገኙበትንና የሚሸለሙበት፣ በሥነምግባራቸው ብልሹ የሆኑት ደግሞ የሚጠየቁበትና በስራቸው የሚጸጸቱበት በመጨረሻም ወደ መልካም ሥነ-ምግባራዊ ባህርይ የሚሸጋገሩበትን እድል ይፈጥራል፡፡

የሥነምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

**ተግባር አራት**

ዓላማ፡ የሥነምግባር ደንብ ሙስናን ለመከላከል ያለውን ፋይዳ ማስገንዘብ ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን አቅርቡ፡፡

ሀ. የሥነምግባር ደንብ ሙስናን ለመከላከል ያለውን ፋይዳ አንድ ተቋም ወስዳችሁ አስረዱ?

ለ. በተቋማችሁ ያሉ የሥነምግባር ደንቦች በተገቢው መንገድ ተግባራዊ እየሆኑ ነው ትላላችሁ? ከሆነ ልምዳችሁን አካፍሉ፤ ካልሆነ ደግሞ ምክንያቱ እና መፍትሄው ላይ ተወያዩበት፡፡

ሐ. በ12ቱ የሲቪል ሰርቪስ የስነ-ምግባር መርሆች ከሙስና መከላከል አንፃር በተቋማችሁ ያላቸው ፋይዳ ላይ ተወያዩ፡፡

### 2.2.3 የውጤት ተኮር ስራ አመራር

የተጠያቂነት አሰራርን በማስፈን ሙስናን ለመከላከል ከሚረዱት ስልቶች መካከል የውጤት ተኮር ስራ አሰራር ተጠቃሽ ነው፡፡ የውጤት ተኮር ስራ አመራር በአንድ መስሪያ ቤት ውስጥ የስራ ቅልጥፍና፣ ግልጽነት፣ የስራ ድርሻ እና ተጠያቂነት እንዲኖር ይጠቅማል፡፡ የውጤት ተኮር አሰራር ሂደት ከግብአት ጀምሮ ያሉትን የስራ ሂደቶች (የውጤት ሰንሰለቶች) ማለትም/የቅርብ ውጤትን (outputs) ፣ የሩቅ ውጤት (outcome) ፣ ፋይዳን (Impact)/ያጠቃልላል፡፡ አሰራሩ በእያንዳንዱ አክቲቪቲ (ስራ) ውስጥ የሪፖርት አደራረግ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ የግድ ስለሚል ተጠያቂነትን ያጠናክራል፡፡ ይህ አሰራር ለቁጥጥር አመቺ ከመሆኑም ባሻገር ደካማ ውጤት (ደካማ አገልግሎት አሰጣጥ) በታየበት አካባቢ ሁሉ የችግሩን ምንጭ (መንስኤ) በቀላሉ ለመለየት ያስችላል፡፡ በመሆኑም ችግሩ የተከሰተው ለሙስና ከሚያጋልጥ ብልሹ አሰራር ወይም ከአቅም ማነስ... ወዘተ እንደሆነ ለማረጋገጥ የሚረዳ በምክንያት የተ ደገፉ መረጃዎችን ለማግኘት ያስችላል፡፡

### 2.2.4 ውስብስብ አሰራሮችን ማቅለል

ብዙውን ጊዜ ደንቦች፣ መመሪያዎች ውስብስብ መሆናቸው፣ እንዲሁም ጉዳይን በማስፈጸም ሂደት ውስጥ የተራዘሙና የተወሳሰቡ አስተዳደራዊ ፕሮሲጆሮች ለሙስና ያጋልጣሉ፡፡ አሠራሮች ውስብስብ እና የተራዘመ ጊዜ የሚወስዱ ከሆነ

ጉዳያቸው በቶሎ እንዲፈፀምላቸው እና ብዙ ሳይደክሙ እንዲቋጭላቸው ባለጉዳዮች ለመንግስት ሠራተኞች ገንዘብ በመክፈል ወይም የመንግስት ሠራተኞች ቶሎ እናስጨርሳለን በማለት ለመደራደር በር ይከፍትላቸዋል፡፡ በመሆኑም የአገልግሎት አሰጣጥን እንደገና በመከለስ (ሪኢንጅነር በማድረግ) የተቀላጠፈ አገልግ ሎትን ማረጋገጥ ሙስናን ለመከላከል ዓይነተኛ ዘዴ እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡

### ተግባር አምስት

ዓላማ፡ ውስብስብ አሰራር ለሙስና በር ከፋች መሆኑን በተግባር እንዲገነዘቡ ማድረግ ቀጥሎ የቀረበውን ሃሳብ አስተውሉና የሚፈለገውን በተግባር አሳዩ፡፡

ሀ. በቡድን ሁኑና አንድ መስሪያ ቤት ጉዳይ ለማስፈጸም ሄዶ በውስብስብ አሰራር ምክንያት የተማረረና ለጉቦ የተጋለጠን ሰው በድራማ መልክ አሳዩ፡፡ ለምሳሌ፡ ከግንባታ ፈቃድ፣ ከጉምሩክ ሥራዎች እና የፍርድ ቤት ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ጉዳይን በማንሳት፡፡

ለ. ከላይ የቀረበውን ድራማ ከተመለከታችሁ በኋላ ውስብስብ አሰራሩ እንዴት እንደተገለጸ አስረዱ፤ ከዚያም ችግሩን ሊያቃልል የሚችል የመፍትሄ ሃሳብ ሰንዝሩ፡፡

### 2.2.5 የሃብት ማሳወቅ

ተጠያቂነትን እንዲሁም ቅንነትን (Integrity) በሲቪል ሰርቪሱ መካከል በማስረጽ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቅሙ መንገዶች መካከል የመንግስት ሰራተኞች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የመንግስት ሰራተኞች ያከማቹት ሃብት፣ ያለባቸው እዳ (ብድር) እንዲሁም የተሰጣቸው ስጦታ በግልጽ እንዲታወቅ ማድረጉ የሙስና ተግባርን በመከላከል ረገድ ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ የሃብት

ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

ለምሳሌ፡ አንድ የመንግስት ሰራተኛ ሃብቱን ባስመዘገበበት ወቅት የስቴሽነሪ ባለቤት እንደሆነ ከታወቀ በሚሰራበት መስሪያ ቤት የስቴሽነሪ ግዢ የማጫረት ስራ ውስጥ እንዳይገባ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ሙስና ተፈጽሞ በተገኘ ጊዜም በሙስና በተጠረጠረው ሰውላይ በቀላሉ ማስረጃ ለማቅረብ ይረዳል፡፡ የሃብትማሳወቅና ማስመዝገብ ተግባር የመንግስትና የግል ሃብት ተለይቶ እንዲታወቅ ስለሚረዳ ግልጽነት እንዲሰፍን ምክንያት ይሆናል፡፡ ህብረተሰቡም የመንግስት ተቀጣሪው ወይም ሹመኛው ከሚያገኘው ገቢ በላይ ያካበተ ከሆነ ሃብቱን ከየት አመጣኸው በማለትሙስናን ለመታገል ይጠቅማል፡፡

የሃብት ምዝገባ ተግባርን ለማስፈጸም የፀረ-ሙስና ተቋማት በማስተባበር ረገድ ኃላፊነት ሊወስዱ ይችላል፡፡ የሃብት ምዝገባን ወቅት እየጠበቁ በየጊዜው ማድረጉም ተገቢ ነው፡፡ ሃብታቸውን የሚያሳውቁ ሰራተኞች በየትኛውም ጊዜ ማረጋገጥ ወይም ማብራሪያ መስጠት ይገባቸዋል፡፡ ባንጻሩ ደግሞ ሃብታቸውን ለማሳወቅ ፈቀደኛ በማይሆኑ እና በሀሰት የሚያስመዘግቡ ሰዎች ላይ ተገቢ ቅጣት መጣል አስፈላጊ ነው፡፡

## ተግባር ስድስት

ዓላማ፡ የሃብት ምዝገባ ሙስናን ለመከላከል ያለውን ፋይዳ እንዲገነዘቡ ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ተወያዩና መልሳችሁን አቅርቡ

ሀ. የሀብት ምዝገባን አስመልክቶ በሃገራችን እየተከናወነ ባለው ተግባርና ጠቃሚነት እንዲሁም ተግዳሮቶቹ እና ተግባራዊነቱን ለማምጣት ምን በደረግ አለበት በሚለው ላይ ተወያዩ፡፡

ለ. የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ የሚከተለውን ይደነግጋል፡፡ አንቀጹ ሙስናን ለመከላከል ያለውን ፋይዳ ተናገሩ፡፡

1. የመንግስት ሰራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ማንም ሰው፡-

ሀ. የኑሮ ደረጃው፣ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ስራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ. ያለው ንብረት ወይም ገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ

የዚህ ዓይነት የኑሮደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ለፍርድቤት ካላስረዳ በቀር እንደሁኔታው የንብረቱ መወረስ ወይም ለመንግስት መመለሱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት መቀጮ ይቀጣል፡፡

### 2.2.6 ምቹ የሥራ አካባቢን መፍጠር

ምቹ የሥራ አካባቢ የሠራተኞችን ደህንነት፣ እድገትና ስኬት የሚያረጋግጥ የሥራ አካባቢ ማለት ነው፡፡ ሠራተኞችን ያላቸውን ከፍተኛ አቅም ተጠቅመው እንዲሠሩ ምቹ የሠራ አካባቢ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

ሰራተኞችን ማበረታታት ሙስናን ለመከላከል እንደ አንድ ጠቃሚ ርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ሰራተኞች በምን ዓይነት ሥነምግባር ተገልጋዮቻቸውን ማስተናገድ እንዳለባቸው በየጊዜው ሊሰለጥኑ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ስራን(ሜሪትን) መሰረት ያደረገ ግምገማ በማድረግ ቅጥርና እድገት በመፈጸም ሰራተኞችን ማበረታታት ተገቢ እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ በእድገትና በዝውውር ላይ ቅሬታ ያለው ሰራተኛ ካለ ባግባቡ ቅሬታው የሚስተናገድበትን መንገድ ማመቻቸትም ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ሠራተኞች ከሚሠሩት የሥራ

ክብደት እና የአዕምሮ ጥረት አንፃር ተመጣጣኝ የሆነ፣ በሥራ ላይ ሊያቆያቸው እና ሊያኖራቸው የሚችል ክፍያ እንዲያገኙ ማድረግ ወዳልተገባ ተግባር እንዳይገቡ በማድረግ ሙስናን ለመከላከል ይችላል፡፡

### 2.2.7 ጠንካራ ተቋማዊ ባህልን ማዳበር

ተቋማዊ የአሰራር ባህል በአንድ ተቋም ውስጥ ስራዎች እንዴት እንደሚከናወኑ የሚያመለክት ነው "Organizational culture is the way things are done around here".ተቋማዊ የአሰራር ባህል በተቋሙ ሰራተኞች ላይ ከሚያሳድረው ተጽእኖ የተነሳ ሙስናን ለመከላከል የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ አለው፡፡ በጠንካራ የስራ ባህል ባለው ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች በተቋሙ ውስጥ ገዢ ለሆነው እና አብዛኛው ሰው ለሚተገብረው ባህል ተገዢ እንዲሆኑ ይገደዳሉ፡፡ ስርዓተ አልበኝነት በሚፈቅድ ወይም ብልሹ አሰራርን ቸል የሚል ባህል ባለበት ተቋም ውስጥ ሙስና የመከሰቱ አጋጣሚ ሰፊ እንደሆነ አንዳንድ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ተቋማዊ ባህል በሂደት የሚገነባ ሲሆን ለተግባራዊነቱ ደግሞ ሰራተኞች፣ ሃላፊዎች፣ ባለድርሻ አካላት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ በተለይ ደግሞ የበላይ አመራር አካላት ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ የሃላፊዎች ግለሰባዊ ስብእና በተቋም ውስጥ መልካም ስነምግባርን ለመገንባት ትልቅ ድምጸት (Tone) አለው፡፡ ተቋማዊ ባህል በአንድ ስልጠና ወይም ልምምድ የሚመጣ አይደለም፤ ይልቁንም በጊዜ ሂደት ውስጥ አሰራርን ልማድ በማድረግ ዘወትር በመተግበር ይመጣል፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ ሙስና እንዲያቆጠቁጥ ሊያደርጉ ከሚችሉ ጎታች የስራ ቦታ ባህል መካከል የሚከተሉት አመለካከቶች ይጠቀሳሉ፡-

- ሁል ጊዜ የተለመደ ተግባር ስለሆነ ስጦታ፣ የመዝናኛ ግብዣ መቀበል… ወዘተ ችግር የለውም፤
- ሙስና በፈጸሙ ሰራተኞች ላይ የሚወሰድ ቅጣት ስለሌ ለሙስናን ማጋለጥ ችግር ፈጣሪ ከመባል ውጭ የሚፈይደው ነገር የለም፤

- ይህን ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ የሚችለው እኔ ሳልሆን ሌላ ሰው ነው (የኔድርሻ አይደለም)፤
- የስራ ባልደረባዬ ምንም ቢያደርግ ለአለቃዬ አላቃጥርም፤
- ይህን ሚስጥር ባላወጣ ማንም ተጎጂ አይሆንም፤
- አለቃዬ የመስሪያ ቤቱን  መኪና እቤቱ ይዞ ይሄዳል፤ እኔም በምነዳው ገልባጭ መኪና አንዳንዴ ብጠቀምበት ምንም አይደለም፤

**ተግባር ሰባት**

ዓላማ፡ በየመስሪያ ቤቱ ያሉትን ጠንካራ የሥራ ባህል እንዲለዋወጡ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ መልሱ፡፡

1. በምትሰሩበት ተቋም ሙስናን ለመከላከል የሚጠቅሙ ጠንካራ የስራ ባህል ናቸው የምትሏቸውን ዘርዝሩ፡፡
2. በተቋማችሁ ውስጥ ሙስና እንዲያቆጠቁጥ ሊረዱ ይችላሉ የምትሏቸው አመለካከቶች የትኞቹ ናቸው? እንዴትስ ይህን አመለካከት መቅረፍ ይቻላል?

## 2.2.8 ሰራተኞችን እያዘዋወሩ ማስራት

በርካታ ባለ ጉዳዮች በሚበዙበት ተቋም ውስጥ ያሉ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞችን እያዘዋወሩ ማሰራት ሙስና እና የሙስና አጋጣሚዎች እንዳይፈጠሩ ለማድረግ ይረዳል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት በሚሰጡ ሰራተኞችና በደንበኞች መካከል ወዳ ጅነት (clientelism) ጎልብቶ በእርስ በርስ መጠቃቀም ሙስና ሊከሰት ይችላል፡፡ በመሆኑም በተለይ ቁልፍ የሆኑ ጉዳይ ማስፈጸሚያ ቦታዎች ለአንድ ሰው ብቻ ርስት ተደርገው መተው የለባቸውም፡፡

## 2.2.9 የቅሬታ መስተንግዶ ሥርዓት መዘርጋት

ባለጉዳዮች ከአንድ ተቋም ሊያገኟቸው የሚገቡ አገልግሎቶችን በግልጽ ሊያውቋቸው ይገባል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ተቋሙ የዜጎች ቻርተር በማዘጋጀት ለተገልጋዮች ግልጽነትን በመፍጠር፣ መብታቸውን በግልፅ አውቀውና ተረድተው

አገልግሎት ለማግኘት ማሟላት የሚያስፈልጋቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በማሳወቅ፣ የተጠያቂነትን ስርዓት በማስፈንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዩን ህብረተሰብ እርካታ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ተቋሙ ባወጣቸው የአገልግሎት ደረጃዎች መሰረት ተገልጋዩ አገልግሎት የማያገኝ ከሆነ አቤት የሚልበትና ፈጣን መልስ ሊያገኝ የሚችልበት የቅሬታ ማስተናገጃ ስርአት መገንባት ተገቢ ነው፡፡ የቅሬታ መቅበያ ስርአት መዘርጋቱ ብቻ በቂ አይደለም፤ ይልቁንም ስርአቱ ህያው መሆኑን በየጊዜው መከታተል ተገቢ ነው፡፡

## 2.2.10 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት ማለት በስራ ኃላፊነት ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች እራስን፣ ቤተሰብን፣ ዘመድን፣ ድርጅትን ወይም ትውውቅ ያላቸውን ሌሎች ግለሰቦችን በገንዘብ፣ በቅጥር ወይም በተለያዩ መንገዶች ለመጥቀም መሞከር(ማሰብ) ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ከሙስና የሚለየው የጥቅም ግጭት የመንግስት ሀላፊዎችና ባለስልጣናት መንግስታዊና ህዝባዊ ሀላፊነታቸውን ሲወጡ በሚፈጠር ስውር የጥቅም ፍላጎት የተነሳ ውሳኔዎችን በማዛባት እንዲወስኑ በማድረግ ለሙስናና ብልሹ አሠራር መከሰት ቁልፍ ድርሻ ያበረክታል፡፡ ሙስና በግል ወይም በቡድን፣ በፖለቲካ መሪዎች ወይም በቢሮክራቶች ሥልጣንና ኃላፊነትን መከታ በማድረግ፣ የህዝብን ጥቅምና ፍላጐት ለግል ጥቅም የማዋል ነው፡፡ በሌላ በኩል የጥቅም ግጭት ለሙስና መከሰት መንስዔ መሆኑንና ሙስና የተከሰተበት ቦታ ሁሉ የጥቅም ግጭት መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡

በአንድ ተቋም የጥቅም ግጭት ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ማስወገድ ሙስናን ለመከላከል አስፈላጊ እርምጃዎች ናቸው፡፡ ሰራተኞች በሚሰሯቸው ስራዎች የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉትን ለይቶ በሥነምግባር ደንብ ውስጥ ማካተት እንዲሁም ማስልጠን ተግባራዊነቱንም መከታተል ተገቢነው፡፡

ለምሳሌ፡ በመሬት አስተዳደር ስራ ውስጥ ፕላን መርምሮ የሚያጸድቅ ሰራተኛ ለባለጉዳዮቹ ፕላን ለመስራት ውለታ ውስጥ ቢገባ፣ እራሱ የሰራውን ፕላን ራሱ መርምሮ ውድቅ ማድረግ ስለማይችል የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊወድቅ ይችላል፡፡ ስለዚህ ተቋማት እንደነዚህ ዓይነት ጉዳዮችን በመፈተሸ የጥቅም ግጭት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን ማስወገድ ይገባቸዋል፡፡

**ተግባር ስምንት**

ዓላማ፡ የአሰራር ባህል ከሙስና ክስተት ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመገምገም ቀጥሎ የቀረበውን ኬዝ አንብቡና ከግርጌው በቀረበው ጥያቄ ላይ ተወያዩበት፡፡ አቶ ኒኮላ በአስመጪና ላኪ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሃብት ናቸው፡፡ ገንዘባቸውን የሚያዘዋውሩበት የአንድ ባንክ ቅርንጫፍ ደንበኛ ናቸው፡፡ የባንኮቹ ሰራተኞች ስራ ቸውን በትጋት የሚሰሩ በመሆናቸውና እሳቸውንም ያለምንም መጉላላት ስለሚ ስተናግዷቸው ሰራተኞቹ በየአመቱ ለሚያደርጉት ጌት ቱጌዘር (የአንድነት ጊዜ) ሁል ጊዜ የ400,000 ሺህ ብር ስጦታ ያደርጋሉ፡፡ የባንኩ ስራ አስኪያጅ ይህን ጉዳይ በአንድ ወቅት በተደረገውና ራሱ በተካፈለበት የጌት ቱጌዘር ግብዣ ላይ ይሰማል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ሌሎችም የባንኩ ደንበኞች ይህን ባህል ስላወቁ በየአመቱ ለባንኩ ሰራተኞች መዝናኛ ይሆን ዘንድ በየአመቱ የተወሰነ ብር ስጦታ እንደሚሰጡ ተገነዘበ፡፡

ጥያቄ፡ 1. እናንተ በባንኩ ስራ አስኪያጅ ቦታ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?

ጥያቄ፡ 2. በመስሪያቤታችሁ ወይም በምታውቁት ተቋም እንዲህ አይነት ልምድ ካለ ልምዳችሁን እና ሊስከትል በሚችለው ጉዳት ላይ ተወያዩበት፡፡

**ተግባር ዘጠኝ**

ዓላማ፡ አስተዳደራዊ አሰራርና ቁጥጥርን መሰረት ያደረገ ስትራቴጂን በተግባር ለመለማመድ ከዚህ ቀጥሎ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ በአንድ ወቅት የፌ.ሥ.ፀ.ሙ. ኮሚሽን ባጠናው ጥናት አሉ ብሎ ያገኛቸው የአሰራር ግድፈቶች ናቸው፡፡ እነዚህ የአሰራር ግድፈቶች፡-

ሀ. እንዴት ለሙስና እንደሚያጋልጡ፣

ለ. የሚያስከትሉት ጉዳት፤

ሐ. በተቋም ውስጥ እንደነዚህ ዓይነት ችግሮች እንዴት እንደሚለዩ፤ እንደዚህ ዓይነት መሰል ችግሮች እንዳይከሰቱ ለመከላከል ተቋማት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ተወያዩበት፡፡

በተቋም A፡

- የዋጋ ማቅረቢያ/ፕሮፎርማ/ ግዥ ከፍተኛ እንደሆነ ተስተውሏል፤
- ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች የሚጠየቁ የግዥ ፍላጎቶች ለማስፈጸም በቂ በጀት መኖሩ ወይም አለመኖሩ በቅድሚ ያሳይጣራ ፕሮፎርማ እንደሚሰበሰብና ግዥ እንደሚፈጸም ተመላክቷል፡
- ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቁ ግዥዎችን የግዥ ኮሚቴ ሰብሳቢና ታዛቢ ኦዲተር ባልተገኙበት በተደጋጋሚ በሶስት አባላት ብቻ መፈጸሙ ተስተውሏል፡፡

በተቋም B:

- ► የመረጃና የሪፖርት አቀራረብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ደካማ መሆን እንዲሁም በአንዳንድ የሥራ ክፍሎች ውስጥ የሚሰሩ ስራዎች እቅድን መሰረት ያደረገ አለመሆን ተስተውሏል፤
- ► በመስሪያ ቤቱ ያሉ ሁለት የስራ ክፍሎች ተመድበው/ተቀጥረው የሚሰሩ አብዛኞቹ ሰራተኞች ብቃታቸውና ክህሎታቸው አነስተኛ መሆኑ ታይቷል፤
- ► በሁለት የስራ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ለስራቸው የሚጠቀሙበት የሥራ መዘርዝርእንዲሁም ለስራክፍሉ የሚያገለግል የሥራ መመሪያና ማንዋል አለመኖር ከዚህ የተነሳ የሥራ ሃላፊዎች ሥራቸውን የሚመሩት በግልጽ መመሪያ ሳይሆን በልምድ፣በቃል ትእዛዝ እና በማስታወሻ መሆኑ ተስ ተውሏል፡፡

## 2.2.11 የአሰራር ስርዓትን በማጥናት ማስተካከያ እርምጃ መውሰድ

ለሙስናና ብልሹ አሰራር መስፋፋት ምክንያት ከሚሆኑ ጉዳዮች መካከል ግልጽነት የጎደላቸውና ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮች መኖር ዋነኛው ነው፡፡ ሙስና እንዳይፈጸም ለመከላከል ለሙስናና ብልሹ አሰራር በር የሚከፍቱ አሰራሮችን በጥናት በመፈተሽ እና የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

- ❖ የአሠራር ሥርዓት ጥናት ምንነት

መልመጃ 1 ሠልጣኞች ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያላችሁን ምላሽ

ለአሰልጣኙ ግለጹ

1. የአሰራር ሥርዓት ምንድነው? የአሰራር ሥርዓት ጥናትስ?

1.1 ሙስናን ለመከላከል የሚካሄድ የአሰራር ስርአት ጥናት ከሌሎች ጥናቶች በምን ይለያል ብላችሁ ታስባላችሁ?

❖ የአሠራር ሥርዓት ምንድን ነው ? የአሠራር ሥርዓት ጥናትስ ?

የአሰራር ስርአት ስንል /System/ የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል በመተካት የምንጠቀምበት ነው

1. …. a set of ideas, theories, procedures, etc according to which some thing is done.
2. …. a combination of related parts organized into a complex whole.
3. …. a scheme of ideas or principles by which something is organized.
4. …. a method or set of procedures for achieving something.

ከነዚህ ትርጓሜዎች በመነሳት የአሰራር ሥርዓት አንድን ስራ ለመስራት ያሉ መመሪያዎች፣ የስራ ሂደቶች፣በስራው ውስጥ የሚሳተፉ የስራ ክፍሎችን እና የእነኝህ ቅንጅታዊ ድምር ውጤት የሚገለጽበት ሥርዓት ነው ማለት ሲቻል፤

በሙስናና ብልሹ አሰራር ላይ የሚካሄደው የአሰራር ስርአት ጥናት ከላይ በተጠቀሱ የአሰራር ስርአት ነጥቦች ላይ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚዳርጉ ክፍተቶችን ብቻ ለመለየትና እነዚህን ክፍተቶች ለማስተካከል የሚያግዙ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማፍለቅ የሚረዳ ጥናት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

❖ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚካሄድ የአሰራር ሥርዓት ጥናት ከሌሎች ጥናቶች የሚለይባቸው ባህሪያት

የአሠራር ሥርዓት ጥናት እንደማንኛውም የጥናት ምርምር ስራዎች ሁሉ መሰረታዊ የጥናት ዘዴን (Resarch Methodology) መሰረት አድርጎ የሚካሄድ

ቢሆንም አንዳንድ የራሱ የሆኑና የሚለይባቸው አንዳንድ ባህሪያት አሉት፡፡ እነዚህም፣

- ❖ በሙስናና ብልሹ አሰራር ላይ ብቻ የሚያተኮር መሆኑ፣
- ❖ በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ከተለመደው የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ለየት ያለ መረጃ የማሰባሰቢያ ስልትን ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ መኖሩ፣
- ❖ የሙስና ወንጀልን ለመከላከል የሚካሄድ ጥናት እንደመሆኑ ልዩ ሙያዊ ክህሎትና ሥነ ምግባር የሚጠይቅ መሆኑ ናቸው፡፡

**መልመጃ 2**

የምትሰሩበትን ወይም አሰራሩን በቅርብ የምታውቁትን ተቋም ምረጡ፤ የመረጣችሁትን ተቋም መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩባቸውና ምላሻችሁን ለተሳታፊዎች አቀርቡ፡

1. ልዩ ልዩ የአሰራር ስርአቶቻቸውን ለይታችሁ አውጡ፡፡
2. በአሰራር ስርዓታቸው ውስጥ ያሉትን የሥራ ሂደቶችና ዋና ዋና የስራ ደረጃዎች/ተግባራት/ እና የሚመሩባቸውን የስራ መመሪያዎች ዘርዝሩ፡፡
3. በእነዚህ የአሰራር ሥርአቶች ላይ ሊካሄዱ የሚችሉ ሌሎች ጥናቶች የሚያተኩሩበትን ነጥብ ለይታችሁ አቅርቡ፡፡
4. በጥናቶቹ መካከል ሊኖር የሚችለውን ልዩነትና አንድነት በዝርዝር አስቀምጡ፡፡ የአሠራር ሥርዓት ጥናት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ያለው ጠቀሜታ

**መልመጃ 3**

ቀጥሎ የቀረበው አባባል የአሰራር ሥርዓት ጥናት ስላለው ጠቀሜታ የሚያስ ተላልፉትን መልእክት ግለጹ፡፡

- የአሰራር ሥርዓት ጥናት ሙስናና ብልሹ አሰራር ተክስተው ከፍተኛ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ለችግሩ ክፍተት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መርምሮ በማውጣት የመፍትሄ ሃሳቦችን በማቅረብ ችግሮች ከወዲሁ እንዲቀረፉ ለማድረግ የሚያስችል ጥናት በመሆኑ ሙስና ተከስቶ ወይም የተባባሰ ደረጃ ላይ ደርሶ ሊፈጠር የሚችለውን ኪሳራ በማስወገድ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአሰራር ስርአት ጥናት ከተቋማት የዕለት ተዕለት ተግባር ጋር ጎን ለጎን ሊከናወን የሚችል በመሆኑ የተቋማት መደበኛ የስራ እንቅስቃሴ ሳይስተጓጎል ችግሮች እንዳይከሰቱ ለማድረግ በጥናት ላይ የተደገፈ የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብ ያስችላል፣

- ግልጽ የሆነ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የሚፈጠሩ የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮች በቀላሉ እንዲጋለጡ ለማድረግ ያግዛል፣

- የሥነምግባር ትምህርትና ሌሎች የመከላከል ስራዎች የሚያተኩሩባቸውን የሥራ አካባቢዎች ለመወሰን በማስቻልም ረገድ ዕገዛ ያደርጋል፡፡
- የአሰራር ስርአት ጥናት በውጭ ወይም በውስጥ አማካሪዎች ሊከናወን ይችላል፡፡ የማማከር አገልግሎቱም ተቋሙን ካለበት ወይም ሊገጥመው ከሚችል የሙስናና ብልሹ አሰራር ስጋት በመታደግ ውጤታማነቱን

  ለማሻሻል የሚያግዝ አገልግሎት ነው፡፡

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ሙስናን ለመከላከል የሚያስችሉ በርካታ ስልቶች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ስልቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠይቁ አነስተኛ ጊዜ እና ወጪን በመቁጠር ተግባራዊ ባለማድረግ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ከፍተኛ ችግሮችን ለማስተካከል የሚሄድበት ሁኔታ ተጨማሪ ኪሳራ የሚያስከተል በመሆኑ መከላከል ላይ ማተኮር ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ውጤታማ የመከላከል ሥራ ለመስራት ሁሉንም በአንዴ ተግባራዊ ማድረግ ላያስፈልግ ይችላል፡፡ እንደተቋሙ የሥራ ባህሪ ለመተግበር የሚመቹና አስፈላጊ የሆኑ ስልቶችን መምረጥና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### የማጠቃለያ ጥያቄ

በዚህ ክፍል ውስጥ ከተነሱት የሙስና መከላከያ ስልቶች መካከል

- በተቋማችሁ ውስጥ የትኞቹን ተግባራዊ እየተረጉ ይገኛሉ?
- ትግበራው በምን ያህል ደረጃ ላይ ይገኛል?
- የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ክፍል ተሳትፎ እንዴት ይገለጻል?
- ከሙስና መከላከል አንፃር ያመጡት ለውጥ ካለ? ተወያዩበት፡፡

## 2.3 ህግን በማስፈጸም ሙስናን የመከላከል ስልት

ሙስናን ለመከላከል ይጠቅማሉ ከሚባሉ ሌሎች የመከላከያ ስልቶች መካከል ህግን በማስፈጸም ሙስናን መከላከል አንደኛው ነው፡፡ የህጎች ተፈጻሚነት ደረጃ በቀጣይ የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች ላይ የራሳቸው የሆነ ተጽእኖ አላቸው፡፡ በአንድ አገር ውስጥ በሙሰኞች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ከሰሩት ወንጀል ጋር ተመጣጣኝ ካልሆነ ሙሰኞችን ከማበረታታቱም ባሻገር ሌሎች ንጹሃን ሰራተኞችም ሆነ ተገልጋዮች ታማኝ በመሆናቸው የተጎዱ ስለሚመስላቸው በሙስና ፈተና ውስጥ እንዲወድቁ ምክንያት ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የህግ የበላይነት አደጋ ውስጥ

እንዲወድቅ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ ህግን በማስፈጸም ሙስናን የመከላከል ስልትን እንመለከታለን፡፡ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኂላ ሰልጣኞች፡-

- ህግን በማስፈጸም የሙስና መከላከል ጽንሰ ሃሳብን ያብራራሉ፤
- ህግን የማስፈጸም ስልት ጥቅሞችን ይዘረዝራሉ፤

**ተግባር** 1፡ ከዚህ በታች በቀረቡት ጥቄዎች መሰረት በቡድን ተወያዩ

ሃሳባችሁን አቅርቡ፡፡

ሀ. ህግን ማስፈጸም ሲባል ምን ማለት ነው?

ለ. ህግን በማስፈጸም ሙስናን የመከላከል ስትራቴጂ አስፈላጊነት

ምንድን ነው? **የተመደበ ጊዜ፡ 2 ሰዓት**

## 2.3.1 ህግን ማስፈጸም

ህግን ማስፈጸም ሲባል ተቋማት ያወጧቸውን ህጎች በተግባር ተርጉመው ውጤት ማምጣት መቻል ማለት ነው፡፡ ይኸውም የሙስና ወንጀል የሚፈጽም ሰው የሚቀጣ መሆኑን መደንገግ ብቻ ሳይሆን ወይም፣ የሙስና ወንጀል ቢፈጸም የሚመረምርና የሚከስ አካልና ውሳኔ የሚሰጥ ፍርድ ቤት መኖሩ ብቻ ሳይሆን፣ የሙስና ወንጀል የፈጸመ ሰው የሚገባውን ቅጣት ተቀጥቶ እንዲታይ ማድረግ፤ በሙስና ድርጊቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ያገኘው ሀብትና ንብረት ተወርሶ ሙስና መፈጸም ኪሳራ እንደሆነ ፈጻሚው ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ማየትና ከተሞክሮ እንዲማሩ ማድረግ ማለት ነው፡፡

## 2.3.2 የህግ ማዕቀፎች

የህግ ማእቀፎች ሙስናን ለመከላከል እና አጥፊዎችን ለህግ ለማቅረብ የሚደረጉ ጥረቶች በአስተማማኝ ሕጋዊ መሰረት ላይ የተመረኮዘ እንዲሆን አስፈላጊ

መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ይህንኑ ጥረት ለማገዝ በሃገራችን ከወጡትና ስራ ላይ ከዋሉት ህጎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

- ► በ1996 የወጣው የወንጀል ህግ 414/96

ሙስናን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተለይተውና ተዘርዝረው በ23 አንቀጾች አማካኝነት በአንድ አካባቢ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ ቀደም ሲል የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሙስናን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ራሳቸውን ችለውና በቀላሉ ለማጣቀስ በሚቻልበት ሁኔታ አንድ ላይ የተቀመጡ አልነበሩም፤ አንዳንድ የሙስና ወንጀሎችን ለመመርመርና ለመክሰስ የሚያስችሉ አንቀጾች አልነበሩም፡፡

- ► አዋጅ ቁጥር1236/2013 የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

- ►አዋጅ ቁጥር 75/2014 የአዲስ አበባ የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ የወጣ አዋጅ

ሙስና መከላከል ተግባር በአንድ ተቋም ተጀምሮየሚጠናቀቅ ባለመሆኑ ኮሚሽኑ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት የህግ ድጋፍ እንዲኖረው በማድረግ ከፀረ ሙስና ትግል አኳያ በአለም አቀፍ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተማዋን በብቃት እንዲወከል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና ለኮሚሽኑ በተለያዩ አዋጆች የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በአንድ ላይ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና ኮሚሽኑ በከተማ ደረጃ የፀረ ሙስናትግሉን የመምራት እና የማስተባበር ሚናውን ለመወጣት የሚያስፈልገውን የኃላፊነት ወሰን በህግ መደንገግ በማስፈለጉ ወጣ አዋጅ ነው፡፡

- ► የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ 882/2007

በተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ውስጥ ግልፅነት የጎደላቸውን ድንጋጌዎች ግልፅ በማድረግ ማሻሻል እና አዳዲስ ድንጋጌዎችን ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሙስና ወንጀልን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ውስጥ በሙስና ወንጀልነት እንዲካተቱ የተደረጉ የተወሰኑ ህዝባዊ ድርጅት አካላትን በሥነ-ሥርዓትና በማስረጃ ህጉም ማካተት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሙስና ወንጀልን በሚመለከት መረጃ የመሰብሰብ፣ የምርመራ፣ የክስ፣ የክርክር፣ በሙስና የተገኘ ሀብት ወይም ተመጣጣኙን የማገድና የማስመለስ ሥራ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ተሸሻሽሎ የወጣ አዋጅ ነው፡፡

- የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አሰራር ደንብ ቁጥር 8/2015፣ 9/2015፣10/2015 እና 11/2015

ደንቡ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አሰራርን ለመወሰን የወጣ ነው፡፡ በደንቡ ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች መቋቋም፣ ዓላማዎች፣ ተጠሪነት፣ ተግባራት፣ የሥነምግባር መኮንን ሃላፊነት፣ የመንግስት መስሪያቤት ወይም ድርጅት የበላይ ኃላፊ ኃላፊነት፣የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ሰራተኞች ሃላፊነት፣ ቅጥር፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችና የኮሚሽኑ የሥራ የስራ ግንኙነት… ወዘተ ያካተተ ደንብ ነው፡፡

- ሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ 668/2002

የሀብትና ገንዘብ ጥቅሞችን ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ ሕግ በዋነኝነት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋትና ሕዝቡ በመንግስት ላይ ያለውን አመኔታ ለማጠናከር፣ ለሙስናና ብልሹ አሰራር በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ለመዝጋት፣ የመንግስትን አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ለማድረግ፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የመንግስትና የግለሰብ ሃብት ተለይተው እንዲታወቁ እና

በህዝብና በመንግስት መካከል መልካም ግንኙነት እንዲዳብር፣ የመንግስት የሥራ ሃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይቀላቀሉ የሚመሩበትን ግልጽ ስርዓት ለመዘርጋትና የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ እንዲሁም ህዝብ መንግስትን ይበልጥ እንዲያምንና ለመንግስት ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ፕሮግራሞችና እቅዶች ተፈጻሚነት የላቀ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚያግዝ ህግ ነው፡፡

- የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ 699/2003

ህጉ የወንጀል ድርጊቶች ከተፈጸሙ በኋላ ፈጻሚዎቹ ተደብቀው እንዳይቀሩና ህግ ፊት ቀርበው ተገቢወን ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ የህብረተሰቡ ሰላማዊ ኑሮ የሚ ረጋገጥበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ ለወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ መስጠት በኅብረተሰቡላይ ከፍተኛ ስጋት ሊያስከትሉ የሚችሉ ወንጀሎችን በማጋለጥ ወንጀልን ለመከላከል፣ የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች በምስክርነታቸው ወይም በጠቋሚ ነታቸው ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከሚደርስባቸው አደጋና ጥቃት ለመከላከልና ደህንነታቸውን
ለመጠበቅ የጥበቃ ሥርዓቶችን በህግ የሚደነግግ አዋጅ ነው፡፡

- ሙስናን ለመታገል የተቋቋሙ የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽኖች፤ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ኢትዮጵያ

ሙስና አለም አቀፍ ከሆኑ ችግሮች መካከል አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ሙስናን ለመከላለል አለም አቀፍ ትግል ይጠይቃል፡፡ በዚህ ረገድ ባለፉት አሰርት ዓመታት በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጠባቂነትና በአገራት ትብብር የሚመሩ በርካታ የፀረ-ሙስና መታገያ የህግ ሰነዶች ወጥተዋል፤ ኢትዮጵያም ሙስናን ለመታገል ከተቋቋሙ የፀረሙስና ኮንቬንሽኖች ፈራሚ አገር ስትሆን የተለያዩ የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭም አባል ናት፡፡ ከነዚህም መካከል፡- የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን (The United Convention Against Convention)

ሙስና በሁለም አገሮች (በሃብታሙም በደሃውም፤ በትልቁም በትንሹም...) የሚገኝክፉ ክስተት (Evil phenomena) ነው። ይህን ክፉ ጠላት ለመዋጋት በዓለም ላይ ያሉ አገራት ዓለም አቀፍ ስምምነት አድርገዋል። ይህ ስምምነት የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬን ሽን በመባል የሚታወቅ ሲሆን እ.ኤ.አ ዲሰምበር 9/ በ2003 ዓ.ም በሚክሲኮ ከተማ ተፈርሟል። ስምምነቱ ላይ ከ140 በላይ ሃገሮች ፈርመውበታል። ኮንቬንሽኑ ሶስት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፤እነሱም፦

- ✓ ሙስናን ለመከላከል እና ለመዋጋት የሚወሰዱ እርምጃዎችን ውጤታማነትና ቅልጥፍና ለማጠናከርና ለማበረታታት፣
- ✓ ሙስናን በመወጋትና በመከላከል የሚደረገውን ዓለም አቀፍ ትብብር ለማበረታታት፣ ለማሳለጥ እንዲሁም የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ፣
- ✓ የህዝባዊ ጉዳዮች (Public affairs) እና የህዝብ ሃብትን በተመለከተ ቅንነት፣ተጠያቂነት እንዲሰፍን እንዲሁም ተገቢ አስተዳደር እንዲኖር መደገፍ የሚሉት ናቸው።

► የአፍሪካ ሕብረት ሙስናን የመከላከያ እና የመዋጊያ ኮንቬንሽን

(AFRICAN UNION CONVENTION ON PREVENTION AND COMBATING CORRUPTION)

ሙስና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል በመሆኑ ሙስናን የማጥፋት ትግል በአንድ አገር ጥረት ብቻ የሚታገሉት ወንጀል አይደለም። ይህን የተገነዘቡት የአፍሪካ አገራት በአህጉሩ ያለውን ሙስና ለመታገል የሚያስችል የጋራ ስምምነት (ኮንቬንሽን) ሞዛምቢክ ማፑቶ ውስጥ እ.ኤ.አ ሐምሌ 11/2003 ላይ ተዘጋጅቶ በ2006 ነሐሴ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። ስምምነቱን 53 አገሮች የፈረሙበት ሲሆን 31 አገሮች ደግሞ አጽድቀውታል (ratified) የኮንቬንሽኑ ዓላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፦

- በመንግስትና በግሉ ዘርፍ የሙስና እና ተዛማጅ ወንጀሎችን በመከላከል፣ በመመር መርና ወንጀለኞች እንዲቀጡ በማድረግ በእያንዳንዱ አገር ልማት እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ማድረግ፤
- በአገራት መካከል ትብብርን በማጠናከርና በማሳለጥ በአፍሪካ ውስጥ ሙስናን ለመከ ላከል፣ ለመመርመርና ወንጀለኞችን ለመቅጣት እንዲሁም ሙስናን ለማጥፋት የሚወሰዱ እርምጃዎችን ውጤታማነት ማረጋገጥ፤
- በክፍለ አህጉሩ ሙስናን ለማጥፋት፣ ለመከላከል፣ ለመመርመርና ወንጀለኞችን ለመቅጣት በየአገሩ የሚወጡ ፖሊሲዎችና አዋጆች እንዲጣጣሙ ለማድረግ ማስተባበር፤
- የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች እንዲረጋገጡ እንቅፋቶችን በማስወገድ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እድገቶች እንዲፋጠኑ ማድረግ፤
- በህዝባዊ ጉዳዮች (Public Affairs) ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር አስፈላጊውን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡
- ኮስት ኢትዮጵያ (Construction Sector Transparency Initiative Ethiopia) በአለም አቀፍ ደረጃ በግንባታው ዘርፍ ሙስናን ለመከላከል ሲባል የተቋቋመ ኢኒሼቲቭ ነው፡፡

### 2.3.3 ህግን የማስፈጸም ስትራቴጂ ጥቅሞች

በሙስና ወንጀለኞች ላይ የሚፈፀም የእርምት እርምጃ የተፈጠሩ ችግሮችን ከማስተካከል ባሻገር ወደፊት የሚፈጠሩ ችግሮች እንዳይከሰቱ ለማድረግ ያግዛሉ፡፡ ይኸውም፣

- በችግሩ ፈጣሪዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ራሳቸውን አጥፊዎችንና በዙሪያው ያሉ ሰዎችን ስለሚያስተምር፣

- የሚወሰደው እርምጃ ከአስተማሪነት ባለፈ ስጋት ስለሚፈጥር የወደፊት አጥፊዎችንእጃቸውንእንዲሰበስቡስለሚያደርግ፣
- “ጥፋተኞችን የሚጋለጡ ደረጃ በተጠናከረና የቅጣቱ ህመም በበረታ ቁጥር የወደፊት የማጥፋት ፍላጎት እየቀነሰ ይሄዳል”

### 2.3.4 የቅጣት ዓይነቶች እና ሙስናን ከመከላከል አንጻር ያላቸው ፋይዳ

በሙሰኞች ላይ የሚደርሱ ቅጣቶችን በሶስት ክፍሎ ማየት ይቻላል ይኸውም፡-

ሀ. በተቋም ደረጃ ሙስኞችን በአግባቡ አጋልጦ ለማውጣት የሚያስችል ስርአት በመዘርጋት በሚያጋጥሙ የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮች ሁሉ ተገቢውን አስተዳደራዊና የዲስፕሊን እርምጃ በወቅቱ መውሰድ፡፡ ለእነዚህ እርምጃዎች የማንኛውንም የፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይጠብቁ ወይም ሳይከተሉ ሊፈጸሙ የሚችሉ ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ ወደፊት በተቋሙ ውስጥ የሚፈጸሙ ሙስና ወንጀሎች እንዳይበረታቱ ያደርጋቸዋል፡፡

ለ. ከዚህ ባለፈ እንደጉዳዩ ክብደት ለሚመለከተው የፍትህ አካል በማቅረብ ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ማድረግና የሚመለከታቸው አካላትም ይህን ውጤታማ ለማድረግ በጥንካሬ በመንቀሳቀስ ሙስኞች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር ያካበቱት ህገወጥ ንብረት እንዲነጠቅ ማድረግ፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ተግባር በሙስና የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት የትም እንደማያደርስ ትምህርት ስለሚሰጥ ሙስናን እንዳይበረታታ ያደርጋል፡፡

በዚህ ረገድ በሀገራችን የፋይናንስ መረጃ ማእከል መቋቋሙ ያለውን ፋይዳ ማስተዋል ይገባል፡፡ ተቋሙ በአዋጅ ቁጥር 657/2002 የተቋቋመ ሲሆን ዓላማውም በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት የሚመለከታቸውንባለድርሻ አካላትን የማስተባበር የሚደርሱትን መረጃዎች የመተንተንና የማሰራጨትና ስራዎችን ማከናወን ነው፡፡

ሐ. በሚከናወኑ ትምህርትና ስልጠናዎች ማህበረሰቡ የሙስናድርጊትን አምርሮ በመጠየፍ ለሙሰኞች በሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት ምክንያት የሚፈጥረው የስነልቦና ቅጣት በራሱ ለሙስና ድርጊት ያለውን ፍላጎት በመቀነስ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይታመናል፡፡

- የሙስና ወንጀል እንደ ወንጀሉ ክብደት ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ጀምሮ እስከ ሃያአምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራትና 200,000 ሺህብር በማይበልጥ መቀጮ ሊያስቀጣ ይችላል፡፡

## 2.4 ግንዘቤን በማሳደግ ሙስናን የመከላከል ስልት

> A fully aware, well informed and properly trained population is the best guarantee of safety and of successful response to any disaster. (UNESCO, 20060)

ግንዛቤ ማስጨበጥ (Raising awareness) አንድ ማህበረሰብ ወይም ኮሚኒቲ ስለአንድጉዳይ ወይም ርእስ መረጃ በመስጠት ወይም በማስተማር አመለካከቱ፣ እምነቱና ባህርይው ላይ ተጽእኖ በመፍጠር ወደ አንድ ወደ ተፈለገ ግብ ማድረስ (ማምጣት ነው)፡፡ ግንዛቤ ማስጨበጥ ታስቦበትና ታቅዶ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ በሌላ በኩልም ግንዛቤ ማስጨበጥ በህብረተሰብ ውስጥ የአንድን ነገር ክፋትም ሆነ በጎነት አጉልቶ የማሳየት ወይም የማሳመን ሂደትነው፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ፣ አተገባበሩ ውጤታማ እንዲሆን የተሳ ታፊዎች ፍላጎትና ስሜት ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ እንዲሁም አንድ የግንዛቤ ማስ ጨበጫ ስልትን ከመጠቀም ልዩ ልዩ ዘዴዎችን እያቀላቀሉ መጠቀም የሚፈለገው ውጤት እንዲመጣ ይረዳል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ ልዩ ልዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችንና ፋይዳቸውን እንመለከታለን፡፡

ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኂላ ሰልጣኞች፡-

- ግንዛቤን በማሳደግ የሙስና መከላከል ጽንሰ ሃሳብን ያብራራሉ፤

▶ ግንዛቤን በማሳደግ ሙስናን የመከላከል ጥቅሞችን ይዘረዝራሉ፤

**የተመደበ ጊዜ፡- 2 ሰዐት**

### 2.4.1 ግንዛቤን በማሳደግ ሙስናን መከላከል

የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ሙስናን መከላከል ስትራቴጂ የመልካም ሥነምግባር ምንነትና ጥቅሞች፣ የሙስናን ምንነትን አስከፊነት በማስተማር አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ሙስናን የሚጠላ (የሚያነውር)፣ የሚዋጋ አመለካከት እንዲያዳብር የማድረግ ስልት ነው፡፡

በእርግጥም ሙስናን በብቃት ለመዋጋትና በቁጥጥር ስር ለማዋል ሙስና መጥፎ ነው ብሎ የሚያወግዝና የሚያነውር ህብረተሰብ ሊኖር ይገባል፡፡

እንዲህ ዓይነት አመለካከት በሚፈለገው ደረጃ ባልዳበረበት ሁኔታ ሙስናን በብቃት መዋጋት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ ያህል ሰው መግደል በማንኛውም ሰው አመለካከት የተወገዘ ድርጊት ነው፡፡ ስለሆነም የተወገዘ ድርጊትን የሚፈጽሙ ሰዎች በጣም ጥቂት ሲሆኑ፣ እነዚህም በማጋለጥናመረጃ በመስጠት ህብረተሰቡ ስለሚተባበር ለፍርድ አቅርቦ ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ ወንጀሉ ከፍተኛ አደጋ እንዳይፈጥር መቆጣጠር ይቻላል፤ ተችሏልም፡፡ ይሁንና መግደል መጥፎ አይደለም የሚል አመለካከት ባለው ህብረተሰብ ውስጥ መግደል ወንጀል ነው ቢባልም፣ ድርጊቱን ከመፈፀም፣ ከማስፋፋት ለማቆም አስቸጋሪ ነው፡፡ በአገራችን ህብረተሰቡ ሙስናን በሚመለከት መግደልን እንደሚያነውረውያነውረዋል ወይ? አንድሰው ከቤቱ ገብቶንብረቱን እንደሚሰርቀው በሙስናም የራሱ ንብረት እንደሚሰረቅ ይረዳል ወይ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ አይደለም ነው፡፡ በእርግጥ እስካሁን እየተደረጉባሉት እንቅስቃሴዎች ሙስናመጥፎ ተግባርእንደ ሆነ በተወሰነ ደረጃ ግንዛቤ መፍጠር ቢቻልም፤ ህብረተሰቡ አሁንም ሙስናን እንደመግደልና መስረቅ የሚያነውርበት ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት አይቻልም፡፡ እንዲያውም “ሲሾም ያልበላሲሻር ይቆጨዋል” የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ለረጅም ጊዜ እንደተግባራዊ

የመኖር መሳሪያ ተደርጎ ይቆጠር የነበረው ስር የሰደደ ብሒል ጨርሶ ተወግዷል ማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ህብረተሰቡ ሙስናን እንደመግደልና ከቤቱ እንደሚሰረቅ አድርጎ እንዲረዳውና ሙስና ስጋት የማይሆንበት ደረጃ እንዲደርስ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራው ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

### 2.4.2 የግንዛቤ መፍጠሪያ መንገዶች

የግንዛቤ መፍጠሪያ መንገዶች ልዩልዩ ቢሆኑም የተለመዱት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

- ከህብረተሰብ ጋር በሚደረጉ ማህበራዊ ስብሰባዎች፣ ወርክሾፖች፣ ጥናታዊ ጽሁፎች፣
- በተደራጀ መልኩ በትምህርት ቤት፣ በኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚሰጡ ትምህርትና ስልጠናዎች፣
- በቤተ መጻህፍት የሚቀመጡ ጽሁፎችን ማዘጋጀትና በትምህርት ቤት ፣በኮሌጆች ውስጥ እንዲቀመጡ በማድረግ ተማሪዎች ግንዛቤያቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ፤
- በቋሚና በተንቀሳቃሽ ኢግዚብሽኖችን በማሳየት ግንዛቤን ማስጨበጥ፤
- በህትመት ማቴርያሎች (ብሮሽር ፣በራሪ ወረቀቶች፣ ቢልቦርድ፣ የካርቱን ስእሎች፣ ፖስተሮች፣ ማኑዋሎች)፣
- ኦዲዮ ቪዲዮ (የቴፕ ካሴት፣ ሲዲ፣ ቪሲዲ፣ ዲቪዲ)፣
- በዌብ ሳይት፣ ኢሜል፣ በሞባይል ላይ መልእክት ማስተላለፍ፣
- ማስሚዲያ (ጋዜጦች የሚወጡ መጣጥፎች፣ መጽሔቶች፣ ራዲዮ፣ ቴሌቭዥን፣
- ታዋቂ ሰዎች ንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

- በስነቃሎች፣ በትውፊቶች፣ በታሪኮች፣ ድራማዎች፣ ግጥሞች፣
- በህዝብ ግንኙነት ስራዎች፣
- በፖለቲካዊ ቅስቀሳዎች (Political advocacy)

አስታውስ አንድብቸኛ የግንዛቤ መፍጠሪያ መንገድ ከመጠቀም ይልቅ ልዩልዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ መንገዶችን ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ ግንዛቤን ማዳበር ይቻላል፡፡

### 2.4.3 ግንዛቤን ማዳበር ሙስናን ለመከላከል ያለው ፋይዳ

የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር ሙስናን በመከላከል ሂደት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ጥቅሞች አሉት፤ ከነዚህም መካከል፡-

- ሙስና ከመፈጠሩ በፊት መከላከል ያስችላል፤ በዚህም በሙስና የሚመዘበረውን ሃብት እንዲሁም ጥፋተኞችን ለማስቀጣት የሚባክነውን ወጪ ያስቀራል፤
- ሙስና ሲፈጠር ወይም ሊፈጠር ሲል ጠቋሚዎችን ማግኘት ያስችላል፤
- በመንግስት መዋቅር የተሻለ አገልግሎት እንዲገኝ ይረዳል፤ በዚህም መልካም አስተዳደር እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡
- በህብረተሰቡ ውስጥ መልካም እሴቶች እንዲገነቡ ያደርጋል፡፡

### 2.4.4 ግንዛቤን ለማሳደግ በልዩ ልዩ አካላት ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎች

**ሀ. በመንግስት ተቋማት**

- ✓ የተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ግልጽ አድርጎ ማሳወቅ፣
- ✓ ቅሬታ ማስተናገጃ ስርአትን ባግባቡ መዘርጋት፣

✓ ህብረተሰቡ ሙስናን በሚታገሉ ተቋማት ላይ አመኔታ እንዲኖረው በሙስና ዙሪያ ጥናት እያደረጉ ማሳወቅ፣

✓ መረጃ ያለምንም ችግር የሚመቻችበትን መንገድ ማዳበር (ማመቻቸት)፤

**ለ. ህጋዊ ማእቀፍ**

✓ **ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት**

✓ **የሚዲያ ነጻነት**

✓ የመረጃ ነጻነት

✓ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ውስጥ በዲሞክራሲያዊ መብቶች ስር በአንቀጽ 29 የአመለካከት እና ሀሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት ስለዚሁ ጉዳይ የሚገልጽ ነው፡፡

**ሐ. የግሉ ማህበረሰብ**

✓ የንግዱማህበረሰብየሙስናተሳታፊ እንዳይሆን በተለያየ መንገድ ማስተማር፤

✓ የሥነምግባር ደንብ በማዘጋጀት የንግዱ ማህበረሰብን የሥነምግባር ደረጃ ከፍ ማድረግ፤

**መ. ሲቪል ሶሳይቲ**

✓ በማስተማር ወይም ግንዛቤን በማስፋት ተሳትፎ ማድረግ፤

✓ ሙስናን በመታገል የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ትስስር መፍጠር፡፡

**ሠ. የሚዲያ ተቋማት**

✓ ነጻ፣ ተፎካካሪ፣ ገለልተኛና በምርመራ ጋዜጠኝነት ሙያዊ ብቃት ያለውየሰው ሃይል እንዲኖር መስራት፣

- ✓ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፣
- ✓ አዘጋጆች እና ኢዲተሮች የጋዜጣ ባለንብረቶች ተመጣጣኝ (Balanced) ሪፖርት እንዲያቀርቡ መርዳት (ማድረግ)

**ተግባር 14**

ዓላማ፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶች፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ላይ ግንዛቤን ማዳበር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቄዎች በቡድን በመሆን ተወያዩባቸው፡፡

1. በአካባቢያችሁ ወይም በተቋማችሁ ለግንዛቤ ማስጨበጫ የምትጠቀሙባቸው መንገዶችን ዘርዝሩና ባስገኙት ፋይዳ ላይ ተወያዩ፡፡
2. ከላይ ከተዘረዘሩት የግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶች መካከል ይበልጥ ጠቃሚ ናቸው የምትሏቸውን አምስት መንገዶች ዘርዝሩና ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. በኢትየጵያ ቴሌቭዥን ከፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ የሚቀርቡ ስፖቶች ግንዛቤን ከማስጨበጫ ጠቀሜታቸው አንጻር ባላቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎን ላይ ተወያዩ፡፡

## 2.5 በብሄራዊ የትስስር ስርዓት ሙስናን የመከላከል ስልት

ሙስናን ከመታገያ ስትራቴጂዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ብሄራዊ የትስስር ስርዓት (National Integrity system (NIS)) በመባል የሚታወቀው ስትራቴጂ ነው፡፡ ይህ ስትራቴጂ ብዙ ተቋማትን የሚያሳትፍ ሁሉን አቀፍ (holistic) የሆነ፣ ባለብዙ ደረጃዎች እና ሁሉን አቀናጅቶ የሚያስተባብር ዘርፈ ብዙ ስትራቴጂ ነው፡፡ NIS በመባል የሚታወቀው የመታገያ ስትራቴጂ ዲዛይን የተደረገው በትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ነው፡፡ ዓላማውም ሙስናን በስፋትና በቅንጅት በመዋጋት በቁጥጥር ስር በማድረግ መልካም አስተዳደርን ማስፈን፤ በዚህም የህብረተሰብ ጥቅም እንዲከበር ማድረግ ነው፡፡ የመታገያ ስትራቴጂውን ግልጽ ለማድረግ ስርአቱ በተለያዩ አምዶች (Pillars) በተገነባ የግሪክ ቤተመቅደስ አምሳያ ቀርቧል፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ በቤተመቅደሱ አምሳያ የተገነባውን ስእል መሰረት በማድረግ ሙስናን የመታገያ ስትራቴጂ የሆነውን የብሔራዊ ትስስር ስርዓትን እንመለከታለን፡፡ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ሰልጣኞች

1. የብሔራዊ የትስስር ስርዓት መሰረተ ሃሳብን ያብራራሉ፤
2. ሙስናን ለመከላከል የብሄራዊ ትስስር ስርአት ፋይዳ ይዘረዝራሉ፤ 3. የብሔራዊ የትስስር ስርዓት ውስጥ የተዋቀሩት አምዶች ሙስናን ከመዋጋት አንጻር ያላቸውን ሚና ይገልጻሉ፡፡
4. ሙስናን ለመዋጋት የብዙ አካላት ተሳትፎና ቅንጅት ወሳኝ መሆኑን

ያስረዳሉ፡፡ የተመደበ ጊዜ፡ 3 ሰዓት

## 2.5.1 ብሄራዊ የትስስር ስርዓት ጽንሰሃሳብ

**ተግባር፡** 10

**ዓላማ፡** ስለብሄራዊ የትስስር ስርዓት የሰልጣኞችን ቀደምት እውቀት እንዲጠቀሙ ለማድረግ

ሀ. የብሄራዊ የትስስር ስርኣት (National Integrity System) ምን ማለት እንደሆነ ግምታችሁን በቡድን ተወያይታችሁ አቅርቡ፡፡

ለ. ከትምህርቱ በኋላ ግምታችሁን እና ያገኛችሁትን ግንዛቤ አወዳድሩ፡፡

የብሄራዊ የትስስር ስርዓት ሃላፊነትና ስልጣንን በማከፋፈል እና ተጠያቂነትን ጎናዊ (horizontal accountability) የማድረግ ስትራቴጂ ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ጠባቂውም ተጠባቂው ሁለቱም ቁጥጥር ያደርጋሉ፤ ቁጥጥርም ይደረግባቸዋል፡፡ በመሆኑም ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ስትራቴጂ ዘመን ያስቆጠረው "ጠባቂውን ማን ይጠብቀዋል?" የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው ይባላል፡፡ ስትራቴጂው በተለያዩ የመንግስት አወቃቀር ላይ ቼክ ኤንድ ባላንስን በመፍጠር ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሚያደርግ ነው፡፡ በተጨማሪም ሙስና

በአጠቃላይ የመንግስት አሰራር ሥርዓት ሪፎርም ውስጥ እንዲፈተሽ የሚያደርግ ስትራቴጂ ነው፡፡ በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ የሲስተም መዳከም ለሙስና በር ይከፍታል ተብሎ ይታሰባል፤ በመሆኑም ስትራቴጂው ለሙስና መከሰት ምክንያት ተጠያቂ የማድረግ ትኩረቱ ከግለሰቦች ይልቅ የአሰራር ስርዓት ላይ ነው፡፡

የዚህ ስርዓት የመጨረሻ ግብ የህብረተሰቡን መልካም እሴቶች በማዳበር፣ ንቃተ ህሊናቸውንም በማሳደግ እንዲሁም የልዩ ልዩ አካላትን ቅንጅታዊ ተሳትፎ በማዳበር (በማረጋገጥ) ቀጣይነት ያለው ልማት፣ የህግ ልእልና እና ጥራት ያለው ኑሮ እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡ ሙስናን በመከላከል ረገድም ሙስናን የጋራ ጥረት እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባል፤ በተጨማሪም ስርዓቱ “ሙስናን ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል፤ እንዲሁም ዝቅተኛ ትርፍ ያለው
(“high risk” and “low return”) እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡” ብሄራዊ የትስስር ስርዓቱ ሙስና ተፈጽሞ አጥፊዎችን ከመቅጣት ይልቅ፣ ከመከሰቱ በፊት መከላከል ላይ ያተኩራል፡፡

**ተግባር 11፡**

> **ዓላማ፡** ጠንካራ የአሰራር ስርኣት ሙስናን ለመከላከል ያለውን ፋዳ ለማስገንዘብ በቡድን ተከፋፈሉና ከዚህ በታች በ”ሀ” እና በ ”ለ” ስር በቀረበው ሃሳብ ተከራከሩ፡፡

ሀ. ሙስናን ለመከላከል ትኩረት ማድረግ የሚገባን የአሰራር ስርዓት ላይ ነው፤

ለ. ሙስናን ለመከላከል ትኩረት ማድረግ ያለብን የግለሰቦች ሥነምግባር እና ችሎታ ላይ ነው፡፡


### 2.5.2 የብሄራዊ ትስስር ስርዓት ስእላዊ መግለጫ እንድምታ

የብሄራዊ ትስስር ስርዓት በግሪክ ቤተመቅደስ ስእላዊ መግለጫ፡፡ ቤተ መቅደሱ በተለያዮ አምዶች ተዋቅሮ የቆመ ጣራ አለው፤ ይህም ብሄራዊ ትስስርን (nation’s integrity) ይወክላል፡፡

ጣራውም የተዋቀረው ትክክል ሆነው በተለያዩ ቦታዎች በቆሙ አምዶች (pillars) ነው፤ እያንዳንዱ አምድ በራሱ የቆመ ቢሆንም አንዱ ሌላውን ለመደገፍ አስተዋጽኦ አለው። ከጣራው በላይ ሶስት ድቡልቡል ኳሶች አሉ፤ እነሱም የህግ ልእልናን (Rule of Law)፣ ጥራት ያለውኑሮን (quality of life) እንዲሁም ዘላቂ ልማትን (sustainable development) ይወክላሉ። (እነዚህ ኳሶች ጣራው ትክክል እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው በጣራው ላይ ጸንተው የሚቆዩት (ከጣራው የማይወድቁት)። በቤተ መቅደሱ አንድ ጎን ያሉት አምዶች ተቋማትን ማለትም ፓርላማን፣ ህግ አስፈጻሚን፣ ፍርድ ቤትን፣ ሙስናን የሚከታተል ተቋምን፣ …. ሲወክሉ፣ በሌላኛው ጎን ያሉት አምዶች ደግሞ ተቋማቱ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉባቸውን መሳሪያዎች ማለትም የመናገር መብትን፣ የመደራጀት መብትን ይወክላሉ።

በስእሉ ላይ እንደሚታየው ቤተመቅደሱ ያረፈበት (የተገነባበት) ወይም ጸንቶ የቆመበት መሰረት ይታያል፤ ይህም የህዝቡን ግንዛቤ (public awareness) እና የህብረተሰብን እሴቶችና ልማዶች (society's values) ይወክላል።

# የግሪክ ቤተ መቅደስ ስእልና እንድምታው




**ስእል1፡ የብሄራዊ ትስስር ስርዓት**

እንግዲህ ከስዕሉ መገንዘብ እንደሚቻለው ቤተመቅደሱ እንደ ቤት የተሟላ ሆኖ እንዲቆም ቤቱን የመሰረቱት ግብአቶች ጥራትና ጥንካሬ እንዲሁም ትስስር ወሳኝ ናቸው፡፡ ቤቱ ጸንቶ እንዲቆም የመሰረት ጥልቀትና ጥንካሬ አስፈላጊ ነው፤ በመሆኑም የህዝብ ንቃተ ህሊና ማደግ እንዲሁም እሴቶቹ ጠንካራ መሆናቸው የቆሙት አምዶች ጠንክረው እንዲቆሙ ያደርጋል፡፡ ህዝቡ የማይጠይቅ፣ የማይቆረቆር፣ የሚፈጸሙ ችግሮችን ነቅቶ የማይጠብቅ ከሆነ፣ እንዲሁም ሙስናን የሚጸየፍ እሴት ካላዳበረ መሰረቱ ያልጸና ይሆንና የቆሙት አምዶች (ተቋማት) ሥራፈቶች ይሆናሉ፡፡ በሌላ በኩልም በተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች ከህብረተሰቡ የሚወጡ በመሆኑ ጠንካራ እሴት ከሌለው ማህበረሰብ ውስጥ የሚወጡ ሰዎች በተቋማት ውስጥ ገብተው ጠንካራ

ስራ ይሰራሉ ማለት ያዳግታል፡፡ በሌላ በኩልም ህግን በማስከበር የሚሰሩ ፖሊሶች፣ መርማሪዎች እንደሚገባ ካልሰሩ የዳኝነት ስራው ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው እያንዳንዱ ብሔራዊ ትስስሩን የፈጠሩት ግብአቶች በሙሉ የተሳሰሩ መሆናቸውንና የአንዱ መዳከም በሌላው ላይ ተጽእኖ ማሳደሩን ነው፡፡

### 2.5.3 ተቋማዊ አምዶችና ምሉእነታቸው

በተለያዩ አገራት የብሄራዊ ትስስር ስርዓት ውስጥ ያሉ የትስር አምዶች ሊለያዩ ቢችሉም ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የትስስር አምዶች (integrity pillars) ተዘውትረው ይታያሉ፡፡ እነሱም፡-

- ► ህግ አስፈጻሚ (Executive)
- ► ህግ አውጭ/ፓርላማ (Parliament)
- ► ፍርድቤት (Judiciary)
- ► የከተማ አስተዳደር (Mayor office)
- ► የመንግስት ሰራተኛ (Public service)
- ► ተጠቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች/ኦዲተር ጀነራል (“watchdog” agencies/Auditor- General)
- ► እንባጠባቂ፣ ፖሊስ፣ የፀረ-ሙስና ተቋም… ወዘተ (Ombudsman, Police, Anti-Corruption Commission, etc.)
- ► ሲቪል ማህበረሰብ (civil society (including the professions and the private sector)
- ► ማስሚዲያ (mass media)
- ► ዓለም አቀፍ ተቋማት (international agencies)

እነዚህ የተጠቀሱትን አምዶች ምሉዕ (Complement) የሚያደርግ በተለያዩ ተቋማት ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚገቡ ዋናዋና ደንቦች (rules) እና ተግባራት (practices) አብረው ይታሰባሉ፡፡ የእነዚህ ደንቦችና ተግባራት አለመኖር የድክመት አመልካች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላል፡፡

**ቀጥሎ የቀረበው**

ሰንጠረዥ ይህንን ያሳየናል፡፡ ሰንጠረዥ 1 ተቋማዊ አምዶችና አስፈላጊ ደንቦች

| ተቋማዊ አምዶች (Institutional pillar) | የሚያስፈልጓቸው ደንቦች/ተግባራት (Corresponding core rules/practices) |
|---|---|
| ህግ አስፈጻሚ (Executive) | የጥቅም ግጭት ህጎች (Conflict of interest rules) |
| ህግ አውጪ/ፓርላማ (Legislature/Parliament) | ፍትሃዊ ምርጫ (Fair elections) |
| ኦዲተር ጀነራል (Auditor General) | ለህዝብ ሪፖርት (Public reporting) |
| የከተማ አስተዳደር (Mayor office) | |
| የመንግስት ሰራተኛ (Public service) | የአገልግሎት አሰጣጥ ሥነምግባር (Public service ethics) |
| ፍርድ ቤት (Judiciary) | የዳኝነትነጻነት(Independence) |
| ሚዲያ (Media) | የመረጃነጻነት(Accesstoinformation) |
| ሲቪል ማህበረሰብ (Civil society) | የመናገርመብት(Freedomofspeech) |
| እንባ ጠባቂ (Ombudsman) | የማኔጅመንት ሪከርድ (Records management) |
| የፀረ-ሙስና ተቋማት (Anticorruption-commission) | አስገዳጅ ህጎች (Enforceable and enforced laws) |
| የግሉ ዘርፍ (Private sector) | የውድድር ፖሊሲ፣ የመንግስት ግዥ ህግና ደንብ (Competition policy, including public procurement rules) |
| ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ (International community) | ውጤታማ የህግ ትብብር ድጋፍ (Effective mutual legal/judicial assistance) |

**ተግባር 12፡**

ዓላማ፡ በስእል የተገለጸውን የትስስር ስርዓት ይበልጥ ለማገናዘብ

መመሪያ፡ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ መልሱ።

1. በቤተመቅደሱ ውስጥ ካሉት አምዶች የተወሰኑት አጠር ቢሉ ሊያስከትሉ የሚች ለውንጉዳት ከአምዶቹ የተወሰኑትን በመውሰድ አብራሩ።
2. የቤተ መቅደሱ መሰረቶች ምንድን ናቸው? እንዴትስ ጠንካራ መሰረት ይሆናሉ
3. በብሄራዊ ደረጃ የተመሰለውን ቤተመቅደስ በአንድ ተቋም ደረጃ በመመሰል በተቋም ደረጃ ሙስናን ለመከላከል ያለውን እንድምታ ተወያዩበት። የህብረተሰብ እሴት መዳከምን የሚጠቁሙ አስተሳሰቦች፣ ድርጊቶች፣ አባባሎች (በየቋንቋው ውስጥ ያሉም ሳሌያዊ አነጋገሮች) ወስዳችሁ ለብሄራዊ ትስስር ስርዓት መዳከም የሚያሳድሩትን ተጽእኖ የተለያዩ ተቋማትን በመውሰድ አስረዱ።

   1. በሰንጠረዥ አንድ ውስጥ የተጠቀሱት ተቋማት ሙስናን በመከላከል ረገድ ሊኖራቸው የሚገባውን ትስስር ተወያዩባቸው።

   2. የብሄራዊ የትስስር ስርዓት "ጠባቂውን ማን ይጠብቀዋል" የሚለውን ጥያቄ እንዴት ይመልሳል?

## 2.6 የሌሎች አገሮች እና የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ የፀረ-ሙስና ተቋማት አሰራር

### 2.6.1 ሆንግ ኮንግ

ሆንግ ኮንግ እ.ኤ.አ 1948 ሙስናን ለመከላከል ህግ አውጥታ ነበር፤ ይኸው ህግ የኮንግረስ አባላት፣የቢዝነስ ሰዎች፣ እንዲሁም የመንግስት ሃላፊዎች ሙስና ውስጥ ገብተው ቢገኙ በእስርና እስከ 10,000ሺ.ህ የአሜሪካን ዶላር ገንዘብ ሊያስቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል:: በመንግስት ስራ ውስጥ ለ ማንኛውም ሰራተኛ ተገቢ ያልሆነ ሃብት አካብቶ እንደሆነ በሙስና ተጠርጥሮ ሊከሰስ እንደሚችል በ1971

ጉቦን መከላከል በሚል ህግ አውጥታ ነበር፤ በ1974 ደግሞ ሙስናን የሚከላከል (Independent Commission against Corruption (ICAC). የሚል ገለልተኛ የፀረ-ሙስና ተቋም አቋቁማለች። ዛሬ ሆንግ ኮንግ ከብልሹ አሰራር የፀዳ ሲቪል ሰርቫ ንት(የመንግስት ተቀጣሪ ሰራተኞች) ካሉባቸው አገሮች ተጠቃሽ አገርናት።

ተቋሙ (ICAC) የመመርመር፣ በቁጥጥር ስር ማዋል፣ የማገድና በዋስ የመልቀቅስልጣን አለው፤ እንዲሁም የሙስና አስከፊነትን በተመለከተ ህብረተሰቡን የማስተማር ሃላፊነት አለው።

የኮሚሽኑ አወቃቀር ኮሚሽኑ ሶስት ትልልቅ

ዲፓርትመንቶችአሉት፤

እነሱም

- ኦፐሬሽን ክፍል
- ሙስናን መከላከል
- ህዝብ ግንኙነት ናቸው።

የኦፐሬሽን ዲፓርትመንት ጥቆማዎችን ይቀበላል ይመረምራል፤ የህዝብ ግንኙነት ክፍሉ ህብረተሰቡ ሙስናን በመታገል ተሰታፊ እንዲሆን በሙስና አስከፊነት ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ያዳብራል። የሙስና መከላከል ዲፓርትመንት ደግሞ በመንግስት ተቋማት ለሙስና የሚያጋልጡ አሰራሮችን፤ የአሰራር ደንቦችን እየፈተሸ እንዲስተካከሉ ያደርጋሉ። እንዲሁም በተጠየቀ ጊዜ ለግሉ ዘርፍ ሙስና የመከላከል የምክር አገልግሎት ይሰጣል።

- ኮሚሽኑ በህግ ከተሰጡት ዋና ዋና ስልጣኖች መካከል፡-
  - በቁጥጥር ስርማዋል፣ የማገድና በዋስ የመልቀቅ፣
  - ኮሚሽነሩ ወይም ምክትል ኮሚሽነሩ ለሙስና ተጠርጣሪዎች (የግልም ይሁን የመንግስት) በቁጥጥር ስር እንዲውሉ የእስር ትእዛዝ መስጠት ይችላሉ፤
  - ኮሚሽነሩ ወይም ምክትል ኮሚሽነሩ በሙስና የተጠረጠሩሰዎችን የባንክ አካውንት ወይም የገንዘብ ዝውውር ምርመራ እንዲካሄድበት ማድረግ ይችላል፤
  - ኮሚሽነሩ ወይም ምክትል ኮሚሽነሩ ማናቸውም የ(ICAC) ሰራተኛ ከማንም ጉቦ እንዳይቀበል ቃለ ማህላ እንዲገባ የማድረግ ናቸው፡፡
- የመንግስት ሰራተኛ የሥነምግባር ደንብ (Ethics Code of Public Servants)

በሆንግ ኮንግ የመንግስት ሰራተኛው ለሰጠው አገልግሎት ጉቦ እንዳይቀበል፣ ማንኛውንም የግብዣ ስጦታ በምን ሁኔታ መቀበል እንደሚገባው የሚያሳውቅ የስነምግባር ደንብ አለ፡፡

### 2.6.2 ሲንጋፖር

ሲንጋፖር እ.ኤ.አ በ1937 ዓ.ም ሙስናን ለመከላከል አዋጅ አውጥታለች፤ አዋጁ ሙስናን ለመመርመር ለተቋቋመው ቢሮ ዳይሬክተር ጠንካራ ስልጣን ለመስጠት ሲባል እንደገና በ1960 ተሻሽሏል፡፡ እ.ኤ.አ በ1989 ዓ.ም አዲስ አዋጅ በማውጣት ህጉ በሙስና የተገኘ ሃብትን እንዲወረስ ማድረግ አስችሏል፡፡ ሙስና በ1940 እና በ1945 በሲንጋፖር የተስፋፋ ነበር፡፡ የዚያን ጊዜ ሙስናን በመከላከል የሚሰራው የፖሊስ ተቋም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ

በወቅቱ የነበሩት ፖሊሶች ራሳቸው በሙስና የተዘፈቁ ስለነበር ይህን ያህል አጥጋቢ ውጤት አልተገኘም ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ ነበር አንድ ገለልተኛ ተቋም ማቋቋም

ያስፈለጋት፡፡ ሙስናን የሚከላከለው ተቋም Corrupt Practices Investigation Bureau (CPIB) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ዳይሬክተሩ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ነው፡፡ ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፡፡ CPIB የተቋቋመው እ.ኤ.አ በ1952 ዓ.ም ሲሆን፣ ተቋሙ ገለልተኛ ነው፡፡ ዓላማውም በመንግስት ሴክተርና በግሉ ዘርፍ ሙስናን መከላከል ነው፡፡ የቢሮው ዳሬክተር በሙስና ተጠርጣሪን ያለምንም የእስር ማዘዣ በቁጥጥር ስር ማዋል ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል የተያዙ ሰዎች እስከ ሰባት ዓመት የሚደርስ ቅጣት ሊያስቀጣ ይችል ነበር፡፡ CPIB እንደተቋቋመ ማስረጃ ሰብስቦ ሙሰኞችን ለማስቀጣት ከፍተኛ ተግዳሮት ገጥሞት ነበር፤ ለዚህ ደግሞ የወጣው ህግ ደካማ መሆኑ ሲሆንሌላው ከመንግስት ሴክተሩ ተባባሪ የመሆን ፍላጎት ማጣት ነበር፡፡ ከ1959 በኋላ ግን በሙሰኛ ሰራተኞችና ኃላፊዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ አስደንጋጭ መሆን ሲጀምር ህብረተሰቡ በመንግስት ላይ ያለውን አመኔታ ጨምሯል፡ የCPIB ቢሮ ሁለት ዲፓርትመንቶች ያሉት ሲሆን አንደኛው የኦፐሬሽን ዲቪዥን ሲሆን፣ ሌላኛው የስፔሻሊስት ድጋፍ ሰጪ ክፍል ነው፡፡ ሁለቱም ተጠሪነታቸው ለዳይሬክተሩ ነው፡፡ ከቢሮው ዋና ዋና ስራዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

- የመንግስት ሰራተኞችን ቅንነትን የመጠበቅ፣ በግሉ ዘርፍም ከሙስና የጸዳ አሰራር እንዲኖር ማደፋፈር (ማበረታታት)፣
- በመንግስት ሰራተኞች ውስጥ ብልሹ አሰራር መኖሩን መከታተል፤ ብልሹ አሰራር ሲከሰት ለሚመለከተው አካል ሪፖርት በማድረግ የዲስፕሊን እርምጃ ማስወሰድ፣
- ሙሰኞች እንዲቀጡ ማድረግ፤ እንዲሁም በመንግስት ተቋማት ውስጥ የመንግስት አሰራሮችን እየፈተሹ ለሙስና በሚያጋልጡ የማስተካከያ እርምጃዎችን መጠቆም፤

### 2.6.3 የኢትዮጵያ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

► **የኮሚሽኑ ምስረታ**

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ1993ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 235/93 የተቋቋመ ሲሆን፣ አዋጁን ማሻሻል በማስፈለጉ በአዋጅ ቁጥር 433/97 እንደገና 1236/2013 ተሻሽሏል።

- ተጠሪነት፡ ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው።
- የአሰራር ነጻነት፡ ኮሚሽኑ ሙስና ለመከላከል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ ነው።

ዓላማዎች፡ ኮሚሽኑ ዓላማዎች

፩/ የትውልድ ስነምግባር እና የሞራል እሴቶችን በብቃት መገንባት፣

፪/ የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሰራርን መከላከል፣

፫/ ለፀረ ሙስና ትግሉ አጋዥ የሆነ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ህዝቡ የፀረ ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል፣

፬/ በህግ የተሰጡትን ስልጣን እና ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት፣

፭/ በመንግስት መ/ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች የመንግስት ልማት ድርጅቶችና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ሃብት እና የገቢ ምንጮቻቸውን በማሳወቅ፣ በመመዝገብ፣ ተደራሽ በማድረግ፣ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ የግልፅነት እና የተጠያቂነትን ስርዓት መፍጠር ነው።

### 2.6.3 የአዲስ አበባ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

► የኮሚሽኑ ምስረታ

የአዲስ አበባ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2014ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 75/2014 ተቋቋመ

► ተጠሪነት፡ ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ነው፡፡

► የአሰራር ነጻነት፡ ኮሚሽኑ ሙስና ለመከላከል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ ነው፡፡

ዓላማዎች፡ ኮሚሽኑ ዓላማዎች

፩/ የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት የሞራል እሴቶችን በመገንባት የነቃ እና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ኅብረተሰብ መፍጠር፤

፪/ የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሠራርን መከላከል፤

፫/ ነዋሪው የፀረ-ሙስና ትግል ባለቤት እንዲሆን ማድረግ፤

፬/ በጸረ ሙስና ትግል ብልሹ አሰራርን ለማስቀረት ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ሥረዓት ማስፈን፤

፭/ በህግ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት፡፡

**የመረጃ ምንጮች**

የተሻሻለው የፌዴራል የሥነምግባርና የጸረሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97

የተሻሻለው የፌዴራል የሥነምግባርና የጸረሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013

የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባርና የጸረሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 75/2014

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሠራተኞች አስተዳደር ደንብና የሥነምግባር ደንብ (ልታተመ)

የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ (2002)፣ ሳይቃጠል በቅጠል፣ ምእራፍ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ (2001)፣ ሥነምግባር እና ሙስና (የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፍ)፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያድርጅት፣ አዲስ አበባ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2001) ሥነምግባር እና ሙስና (የስልጠና ሞጁሎች)፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2003)፣ ፕሮፋይል፣ ምእራፍ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

African Union Convention on Preventing and combating corruption Retrieved from www.africa-union.org/root/aa/documents

G.KAMESWARI (2006)፣ Anti-Corruption Strategies፣ The ICFAI University press.India.

Richard Sayers. TIsource book (2000). The National Integrity System Retrieved from

www.transparency.org on Dec 23/2012

RobMcCusker: Australian Institute of criminology, Review of anticorruption strategies. Retrieved from www.aic.gov.auon Feb.12.2012

United Nation convention against Corruption Retrieved from www.unodc.org

UN Prevention: An effective Tool to Reduce corruption. Vienna, December 1999 retrieved from www.unodc.org/pdf/crime/gpacpublicationon Mar.12.2012.

UNDRAFT.United Nations Manual on Anti-Corruption Policy, Vienna, June 2001.Retrieved from www.unodc.org/pdf/crime/gpacpublicationon Mar.12.2015

UNESCO Principles of Awareness Raising (2006). Retrieved from www.unesdoc.unesco.org

Boris and Elend (1995) Role of civil society in curbing corruption in countries ofTransitionEconomics.

Black's Law Dictionary (1990) 6th Ed. St Minn. Westpublishing.

Elliott, Rimberly A. (1997) "Corruption" as a Global policy problem over view and Recommendation "In kimberily A. Eliot (ed.) Corruption and the Global Economy. Institute for international Economics, WashingtonD.C.

Jonston, Micael (1997) "public officials, private interests and sustainable

Democracy: connection between politics and corruption." In kimberily A.

Elliot (ed.) corruption and the Global Economy. Institute for International

Economics, WashingtonD.C.

Kato, Damian (1995) Enhancing of ethics, Transparency and Accountability in Uganda. Workshop on civil service reform in Anglophone Africa. Cape Town(Unpublished).

Klitgaard,Robert(1988)Controllingcorruption.UniversityofCaliforniapress.Berkeley.

Korajian, Garnbis (2003) Good Governance, Transparency and Reform measure to EnchanceAccountabilityinEthiopia.Coursemanual(unpublished).

Korea Independent commission againstcorruption (2003) "The Anti-Corruption ACTanditsenforcementDecree"inKICALAnnualReport2002(summary)KICAC.

OECD Anti-corruption Unit. http://WWW.oecd. Org//daf/no corruption /index.htm pope,Jeremy (2005) "Elements of successful Anti-corruption strategy." In Rick stapenhurst and saccr. J. Kpunden (ed.) curbing corruption toward a model for Building national integrity.ED/ development studies. World Bank WashingtonD.C.

Rose-Ackerman, Susan. (1996) "Democracy and 'Grand corruption'". International socialsciencejournal.SpecialIssueoncorruptioninwesterndemocracy.

Stapenhurst, Rick and shar. J.K punden (ed). (1999) curbing corruption To word amodelforBuildingnationalIntegrity.EDIdevelopmentstudies:WorldBank,W as hington D.C.

Stapenhusrt Rick and shahrzad, sedigh. (1999) “An overview of the cost of corruption and strategies to Deal withit.” In Rick stapcnhurs and sahr J. kepunden (ed.) curbing corruption:Tp word a model for Building national Integrity. EDI development studies, World Bank,WashingtonD.C.

Sam Ford, C. (1998) Public sector Ethics founding and implementing values. WashingtonD.C.

Transparency International. (2008) “Where does corruption Flourish” TI source Book. TI,Berlin. (1995) “Building a global coalition against corruption” annual Report. IL, Berlin.(2002) Global corruption Report TL,Berlin.

World Bank (2006) Corruption and Economic Development: Helping countries combat corruption The Role of the World Bank. Washington D.C (1999) Curbing corruption. EconomicDevelopmentInstituteoftheWorldBank,WashingtonD.C

United Nations (1997) UN General Assebly Resolution on corruption http://WWW. Un.Org/ documents/. (1999) The Global program against corruption UN Anti-Corruption Toolkit.

http://WWW.Unodc.Org/unodc/en/corruption.htm